# የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ

## ትምህርት አንድ

# የእምነት አንቀጽ

## The Apostles' Creed
## Lesson One
## The Articles of Faith

ተርጓሚ እሸቴ በለጠ

Biblical Education. For the World. For Free.

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

# እናስተዋውቅዎ

የሰርድ ሚሊኒየም ሚኒስትሪ እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ1997 ዓ.ም. ተመሠረተ፡፡ ይህ አገልግሎት አትራፊ ያልሆነ ድርጅት ሲሆን፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮዎችን ለመላው ዓለም በነጻ ለማዳረስ የተቋቋመ ነው፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለውን ጤናማ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ - መሠረት ያለው ክርስቲያናዊ የአመራር ስልጠና ፍላጎት ምላሽ ለመስጠት፣ ምንም ዓይነት የስልጠና ግብዓቶች የማግኘት እድል ለሌላቸው ክርስቲያን መሪዎች የሴሚነሪ ሥርዓተ-ትምህርቶችን በማዘጋጀት እናሰራጫለን፡፡ ሰርድ ሚሊኒየም ሚኒስትሪ በመላውም ዓለም ለሚገኙ ክርስቲያን መሪዎችና ፓስተሮች የተመጣጠነ ዋጋ ያለው፣ በደጋፊዎች የሚታገዝ፣ ለተጠቃሚው ምቹ፣ በልዩ ልዩ የመገናኛ ብዙሃን ዘዴዎች የታገዘ ሥርዓተ-ትምህርት በአምስት ቋንቋዎች (በእንግሊዝኛ፣ በስፓኝ፣ በራሺያኛ፣ በማንዳሪን ቻይንኛ እና በአረብኛ) አስተርጎሞ አሰራጭቷል፡፡ ሁሉም ትምህርቶች የተጻፉት፣ የተዘጋጁት እና የታተሙት በአገልግሎቱ ውስጥ ሲሆን በ The History Channel©. In 2009 ካሉት ጋር በቅርፅና በጥራት ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ የሰርድ ሚሊኒየም ሥራ ማለትም ጥራት ላለው የማስተማሪያና የአኒሜሽን የቪዲዮ ፕሮዳክሽን ሥራዎቹ ሁለት የቴሊ አዋርድ ሽልማቶችን ተቀብሏል፡፡ የማስተማሪያ ግብዓቶቻችን በዲቪዲ፣ በህትመት፣ በኢንተርኔት ማስተላለፊያ ዘዴዎች፣ በሳተላይት የቴሌቪዥን ስርጭት፣ በራዲዮና በቴሌቪዥን ስርጭቶች ለማቅረብ በሚያስችል መልክ የተቀረፁ ናቸው፡፡

ስለ አገልግሎታችን የበለጠ መረጃ ለማግኘትና እንዴት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆን እንደምትችሉ ማወቅ ከፈለጋችሁ፣ www.thirdmill.org የተሰኘውን ድረ-ገጽ ይጎብኙ፡፡

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

# ማውጫ


1. **መግቢያ**
2. **ታሪክ**

ዕድገት
ዓላማ
    ቅዱሳት መጻሕፍት
    ባህላዊ አስተምህሮዎች
    የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ

3. **ወፍ በረር ዳሰሳ**

እግዚአብሔር
    ሥላሴ
    አካላት
ቤተክርስቲያን
    ተሳትፎ
    ጥበቃ
ድነት

4. **አስፈላጊነት**

መሠረታዊ
    ደረጃ
    አመክንዮአዊ መሠረት
ዓለምአቀፍ
    አዲስ ኪዳን
    የቤተክርስቲያን ታሪክ
    የአሁን ዘመን
አንድነት

5. **ማጠቃለያ**


© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

# 1. መግቢያ

ለመሆኑ ዛፍን ዛፍ ያሰኘው ምንድን ነው? ወይንም ቤትንስ ቤት ያሰኘው ምንድን ነው? ሰውንስ ሰው ያደረገው ምንድን ነው? ወይንም በሌላ መንገድ ጥያቄውን ብናቀርበው፣ አንድን ነገር ዛፍ ወይንም ቤት ከማለታችን አስቀድሞ ምን የጥራት መመዘኛዎች ሊኖሩት ይገባል? ብላችሁ ጠይቃችሁ ታውቃላችሁ? እነዚህን መሳይ ውስብስብ ጥያቄዎች በሺዎች ለሚቆጠሩ ዓመታት ፈላስፎች ሲያወጡና ሲያወርዱባቸው የኖሩ ናቸው፡፡ የክርስቲያናዊ ነገረ-መለኮትን ጥናት ስንጀምረውም ከተመሳሳይ ጥያቄዎች ጋር እንጋፈጣለን፡፡ በመሠረቱ፣ "ክርስቲያን" ተብለው የሚጠሩና አብዛኛዎቹ በብዙ ጉዳዮች የማይስማሙ ስፍር ቁጥር የሌላቸው አብያተክርስቲያናት አሉ፡፡ ስለዚህ "ለክርስቲያናዊ ነገረ-መለኮት ከድርድር ውስጥ የማይገቡና መሠረታዊ አስተምህሮዎች ምንድን ናቸው?" ብሎ መጠየቅ ጠቃሚ ነው፡፡

አሁን፣ ይህንን ጥያቄ ስንጠይቅ ግን አንድ ሰው፣ ምንም እንኳን የነገረ-መለኮት እውቀቱ ደካማ ቢሆንም ሊድን የሚችል መሆኑን ልናውቅና ግልጽ ሊሆንልን ይገባል፡፡ ለክርስቶስ መሰጠታችን በራሱ እኛን ክርስቲያን ለማድረግ ብቁ ነው፡፡ ሆኖም ደግሞ፣ አንድ ሰው "ክርስቲያን" ተብሎ ከመጠራቱ አስቀድሞ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ወሳኝ ሃሳቦች በየትኛውም ነገረ-መለኮታዊ ስርዓት ውስጥ በግልጽ ሊታወቁ ይገባል ማለትም ሚዛናዊነት ነው፡፡ ከቤተክርስቲያን ቀደምት ምዕተ-ዓመታት አንስቶ፣ የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ስለእነዚህ መሠረታዊ እምነቶች ጠቅለል ያለ ጠቃሚ መግለጫ በመስጠት ላይ የሚገኘው ለዚህ ነው፡፡

አሁን በእጃችሁ ያለው ትምህርት፣ በሁሉም ዘንድ በውል የሚታወቀውና በስፋት አገልግሎት የሚሰጥበት *የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ* ተብሎ የሚጠራው ተከታታይ ትምህርት ክፍል አንድ ነው፡፡ *የእምነት አንቀፆች* የሚል ርዕስም ሰጥተነዋል፡፡ ምክንያቱም ራሳቸውን "ክርስቲያን" ብለው በሚጠሩ ሁሉ ዘንድ ሊታወቁና ሁሉ እርግጠኛ ሊሆንባቸው የሚገባቸው የእምነት አንቀጾችና አስተምህሮዎች ጠቅለል ብለው የቀረቡበትን *የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ* እንመለከታለንና ነው፡፡ *የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ* በብዙ ዓይነት ቅርጾች በቀደሙት የቤተክርስቲያን ዘመናት ውስጥ ይገለጥ ነበር፡፡ በ700 ዓ.ም. አካባቢ ግን ደረጃውን ጠብቆ በላቲን ቋንቋ ተዘጋጀ፡፡ እውቅ የሆነው ዘመናዊው የእንግሊዝኛ ቅጂ ትርጉም እንደሚከተለው ይነበባል፡፡

*እኔ ሁሉን በሚችል፣ ሰማይንና ምድርን በፈጠረ በእግዚአብሔር አብ አምናለሁ፡፡*
*ድግሞም በአንድ ልጁ፣*
*በመንፈስ ቅዱስ በተፀነሰ፣*

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

*ከድንግል ማርያም በተወለደ፣*
*በጴንጤናዊው በጲላጦስ ዘመን መከራን በተቀበለ፣*
*በተሰቀለ፣ በሞተ እና በተቀበረ፤*
*ወደ ሲኦልም በወረደ፡፡*
*በሦስተኛውም ቀን ከሙታን በተነሣ፡፡*
*ወደ ሰማይም በወጣ*
*ሁሉን በሚችል በእግዚአብሔር አብ ቀኝ በተቀመጠ፣*
*ከዚያም በሕያዋንና በሙታን ሊፈርድ በሚመለስ፣*
*በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አምናለሁ፡፡*
*ደግሞም በመንፈስ ቅዱስ፣*
*በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን፣*
*በኀጢአት ስርየት፣*
*በሥጋ ትንሣኤ፣*
*በዘላለም ሕይወት አምናለሁ፡፡ አሜን፡፡*

የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫን እንደ እምነት አንቀጻችን በመውሰድ የምናደርገው ውይይት በሦስት የተከፈለ ነው፡፡ በመጀመሪያ፣ ስለ መግለጫው ታሪክ እንነጋገራለን፡፡ ሁለተኛ፣ በውስጡ ስላካተታቸው መግለጫዎች ወፍ በረር ዳሰሳ እናደርጋለን፡፡ ሦስተኛ፣ አስተምህሮዎቹ በእኛ ዘመን በሚኖራቸው ፋይዳ ላይ እናተኩራለን፡፡ *በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ* ታሪክ እንጀምር፡፡

## 2. ታሪክ

የሐዋርያትን የሃይማኖት መግለጫ ታሪክ ስንዳስስ፣ በሁለት ጉዳዮች ላይ እናተኩራለን፡፡ በአንድ በኩል፣ ማን እንደፃፈውና መቼ እንደተጠናቀረ በማንሳት የመግለጫውን እድገት የምንመለከት ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ፣ ቤተክርስቲያን ይህንን መሳይ መግለጫ ልታወጣና ልትጠቀምበት ያስፈለገበትን ምክንያትና ዓላማ እንመለከታለን፡፡ በመጀመሪያ *የሐዋርያትን የሃይማኖት መግለጫ* ታሪካዊ እድገት እንዳስሳለን፡፡

### እድገት

በአንድ ወቅት *የሐዋርያትን የሃይማኖት መግለጫ* በአንደኛው ክፍለ ዘመን ዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ራሳቸው ጽፈውታል ተብሎ ይታመን ነበር፡፡ እንዲያውም መግለጫው ያካተታቸውን ዐሥራሁለት ነገረ-መለኮታዊ መግለጫዎች እያንዳንዳቸው አንድ በማዋጣት ጽፈውታልም ይባል ነበር፡፡ ሆኖም ግን፣ ይህ ስለ መከናወኑም ሆነ የትኛውም ሐዋርያ በመግለጫው የአጻጻፍ ሂደት ውስጥ ስለመሳተፉ የተገኘ ምንም ማረጋገጫ የለም፡፡ ግን ሐዋርያት ካልፃፉት ማን ጻፈው?

*የሐዋርያትን የሃይማኖት መግለጫ በባለቤትነት ፊርማውን አሳርፎ እኔ ጻፍኩት የሚል ስላልተገኘ ማን ጻፈው? የሚለው ነገር ክፍት ነው፡፡ በጣም በእርግጠኝነት እነዚህ ጥያቄዎች በጣም ወደ ኋላ መለስ ብለን ማለትም ከክርስቶስ ልደት በኋላ በነበሩት አርባ ወይንም ሃምሳ ዓመታት ጀምሮ ለመጠመቅ የሚዘጋጁ ሰዎች የሚጠየቁዋቸው ጥያቄዎች እንደነበሩ እናውቃለን፡፡ ስለዚህም፣ አንድ ሰው፣ ሰማይንና ምድርን በፈጠረ በእግዚአብሔር አብ ታምናለህን? ተብሎ ይጠየቃል፡፡ ይህንንም ያወቅነው ብዙ ሰዎች ስለ ጥምቀታቸው ወቅት ሲናገሩ እነዚህን የመሳሰሉ ጥያቄዎችን እንደተጠየቁ ስለሚናገሩ ነው። በ200 ዓ.ም. ተርቱሊያን የቀደምት ሮም የሃይማኖት መግለጫ ተብሎ የሚጠራውንና ከሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ጋር ተመሳሳይነት ያለውን መግለጫ እነዚህን የጥምቀት ጥያቄዎች "ታምናለህ" "ታምናለህ" የሚሉትን አስመልክቶ አጣቅሶት እናገኛለን፡፡ የሐዋርያትን የሃይማኖት መግለጫ አስመልክቶ የምናገኘው የመጀመሪያ ማስረጃ ሩፊነስ በ390 ዓ.ም. ገደማ የሰጠውን ሲሆን፣ እርሱም ታሪኩን እያንዳንዳቸው ሐዋርያት ይሁዳን የተካው ማትያስን ጨምሮ በሃይማኖት መግለጫው ውስጥ ያሉትን እንዳንድ ማረጋገጫዎች ሰጥተዋል ከሚለው ጋር አያይዞታል፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ለዚያ ጽንሰ ሃሳብ ማረጋገጫ የለንም፣ ሆኖም ግን፣ እነዚያ ማረጋገጫዎች ዞረው ዞረው ወደ ሐዋርያት የመመለሳቸው ጉዳይ ግን በእርግጥ ጥሩ መደላደል ይኖረዋል፡፡ (ዶ/ር ጆን አስዋልት)*

በቀደምት ክርስቲያኖች ጽሑፎች ውስጥ፣ ከሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ጋር የሚስማሙ በርካታ መሠረታዊ አስተምህሮዎች ይገኛሉ፡፡ በአንድ በኩል፣ መሠረታዊ የሆኑትን እምነቶች ዘርዘር አድርገው የሚያስረዱ የእምነት ደንቦች አሉ፡፡ የቀደምት አባቶቻችን ጽሑፎች እንደሚያመለክቱን የተጻፉት የእምነት ደንቦች ደንቦቹን የቀረፀችውን ቤተክርስቲያን እምነቶችና ልምዶች ጠቅለል አድርገው የሚያቀርቡ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፣ ኦሪገን *On First Principles* በተሰኘው የመጀመሪያ ሥራው የእምነትን ደንብ ያስገባ ሲሆን፣ ኢራኒየስ ደግሞ *Against Heresies* በተሰኘው ድንቅ የመጀመሪያ መጽሐፉ በምዕራፍ ዐሥር ውስጥ አንዱን አካቷል፡፡ ይህንን የመሳሰሉት የእምነት ደንቦች የቤተክርስቲያንን አስተምህሮ ለመጠበቅ፣ ሕዝቦቿን በተለይም መሪዎችን ለማሰልጠን በዓላማ የሚቀረፁ ናቸው፡፡ አብዛኛውን ጊዜ እነዚህ ደንቦች ከማህበረ ምዕመን፣ ማኅበረ ምዕመን የተለያዩ ይሆናሉ፡፡ በጥቅሉ ግን፣ ደንቦቹ ወሳኝ የሆኑ አስተምህሮዎችን ማረጋገጫዎች እንደዚሁም ግብረገባዊ ትምህርቶችንና ልማዶችን አካትተው ይቀረፃሉ፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ፣ ጥንታዊያኑ አስተምህሮዎች በሃይማኖት መግለጫ መልክ ተዘርዝረው ይቀመጣሉ፡፡ እነዚያም የቤተክርስቲያንን የእምነት ሕግጋት፣ በተለይም ወሳኝ የሆኑትን

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

እምነቶቿን በከፊል ግን ጠቅለል ባለ መልክ በአጭሩ የሚይዙ ናቸው፡፡ እነዚህ ደንቦች አብዛኛውን ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ሥርዓቶች ለምሳሌ እንደጥምቀት በመሳሰሉት መላልሰው ይገለጣሉ፡፡ በመጀመሪያውና በሁለተኛው ምዕተ ዓመታት፣ የዚህ ምክንያቱ እያንዳንዷ አጥቢያ ቤተክርስቲያን የራሷ የእምነት መግለጫ ወይንም ወሳኝ የሆኑትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶች ጠቅለል አድርጋ የምትገልጥበት መንገድ ይኑራት የሚል ሊሆን ይችላል፡፡ በሦስተኛውና በአራተኛው ምዕተ-ዓመታት ውስጥ ግን አንዳንዶቹ የሃይማኖት መግለጫዎች ከዚያ የላቀ ፋይዳ አንግበው በመነሳት በበርካታ አብያተ ክርስቲያናት አገልግሎት ላይ ውለው ነበር፡፡

በዚህ ጉዳይ ስመጥር የነበረው ጥንታዊ የሃይማኖት መግለጫ፣ ከሮሜ ቤተክርስቲያን የወጣውና በተደጋጋሚ የሮሜ የሃይማኖት መግለጫ ተብሎ የሚጠራው ነበር፡፡ ይህ የሃይማኖት መግለጫ ከሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ጋር በጣም የሚመሳሰልና ብዙ ምሁራንም የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ የሮሜ የሃይማኖት መግለጫ ቀደምት ቅጂ ነው በማለት እንዲያምኑ አድርጓቸዋል፡፡

ነገር ግን የዚህን የሃይማኖት መግለጫ ትክክለኛ ምንጭ ከማግኘቱ ባሻገር፣ ከጥያቄው በስቲያ ያለው እውነት ይህ የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ በስፋት በተለይም በምዕራባዊያኑ አብያተክርስቲያናት በጥቅም ላይ የዋለ መሆኑ ነው፡፡ ቀደም ባሉት ምዕተ-ዓመታት፣ የቃላት አጣጣሎቹ ከቤተክርስቲያን ቤተክርስቲያን መጠነኛ ልዩነቶች ነበሯቸው፡፡ ሆኖም በስምንተኛው ምዕተ-ዓመት ዛሬ እኛ በምንገለገልበት ዓይነት ደረጃ ወጥቶለት ተመሳሳይ አጣጣል (አሰዳደር) እንዲኖረው ተደርጎ ተቀረፀ፡፡

ይህንን የሃይማኖት መግለጫውን ታሪካዊ የእድገት ሂደት በአዕምሯችን ይዘን፣ ከሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ አወጣጥና አጠቃቀም በስተጀርባ ያለውን ዓላማ መመልከት ይገባናል፡፡

## ዓላማ

በዘመናችን፣ ብዙ ክርስቲያኖች የሃይማኖት መግለጫዎችን አስመልክቶ ጥርጣሬዎች አሉባቸው የዚህን ምክንያት መረዳቱም አዳጋች አይሆንም፡፡ በጣም ጥቂት ክርስቲያኖች የሃይማኖት መግለጫዎች ከቅዱሳት መጻሕፍት የተስተካከለ ሥልጣን አላቸው ብለው በግልጽ ሲናገሩ፣ ጥቂቶቹ ጤናማ አተያይ ያላቸው ክርስቲያኖች ደግሞ የተወሰኑትን የሃይማኖት መግለጫዎች ከራሱ ከመጽሐፍ ቅዱስ አኩል ያደርጉታል፡፡ ሆኖም የትኛውም የሃይማኖት መግለጫ በጽንሰ-ሃሳብም ሆነ በተግባር ይህንን ወደ መሰለው እርከን ከፍ ሊል አይገባም፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ ብቸኛው፣ እስትንፋሰ መለኮት ያለበት፣ የማይሻር የእምነትና የልምምድ መመሪያችን ነው፡፡ የሃይማኖት መግለጫዎች ግን፣ የቅዱሳት መጻሕፍት መረዳታችንን ጠቅለል አድርገው

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

የሚይዙ የሚሻሩ የማስተማሪያ መሣሪያዎች ናቸው፡፡ አሁን ልንመለከተው ያለውም የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ክርስቲያኖች የመጽሐፍ ቅዱሱን አስተምህሮ ጠንቅቀው እንዲያውቁና በተማሩትም ታማኝ ሆነው እንዲዘልቁ ለመርዳት የተዘጋጀ ነው፡፡

የሐዋርያትን የሃይማኖት መግለጫ ዓላማ በሦስት እርከኖች እንመረምራለን፡፡ በመጀመሪያ፣ ቅዱሳት መጻሕፍት የእውነተኛው አስተምህሮ ምንጭና ማኅደር መሆናቸውን እንመለከታለን፡፡ ሁለተኛ፣ የቤተክርስቲያን ትውፊታዊ አስተምህሮዎች የቅዱሳት መጻሕፍት ማረጋገጫዎች መሆናቸውን እንመለከታለን፡፡ በሦስተኛ ደረጃ ደግሞ፣ የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ትውፊታዊውን የአብያተክርስቲያን የቅዱሳት መጻሕፍት ግንዛቤና መረዳት ጠቅለል አድርጎ ለማቅረብ የተዘጋጀ መሆኑን እንመለከታለን፡፡ የአስተምህሯችን መሠረት ቅዱሳት መጻሕፍት መሆናቸውን አቋመ ጽኑ ክርስቲያኖች ሳያወላውሉ የሚያረጋግጡ የመሆኑን እውነታ በማስረገጥ እንጀምር፡፡

## ቅዱሳት መጻሕፍት

የጥንታዊቱ ቤተክርስቲያን አባት የሆነው ኦሪገን *On First Principles* በተሰኘውና በሦስተኛው ምዕተ ዓለም መጀመሪያ አካባቢ በተጻፈው መጽሐፉ መግቢያ ላይ ያሰፈረውን እስኪ አድምጡ፡

> *ለሚያምን ሁሉ.... ከክርስቶስ ትምህርቶችና ንግግሮች ውጪ ለሰዎች መልካምና ደስታ የምላበትን የሕይወት ምስጢር ሊገልጥላቸው የሚችል ሌላ ምንም ዓይነት ምንጭ የለም፡፡ የክርስቶስ ንግግሮች ስንል ግን ሰው ሆኖ ሲመጣ የተናገራቸውን ብቻ ማለታችን አይደለም... ከዚያ ዘመን ቀደም ብሎም፣ የእግዚአብሔር ቃል የሆነው ክርስቶስ፣ በሙሴና፣ በነቢያት... በተጨማሪም ... ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ በሐዋርያቱ ተናግሯል፡፡*

ኦሪገን ቅዱሳት መጻሕፍት በጠቅላላ የክርስቶስ ቃሎች መሆናቸውን እና የእውነተኛ አስተምህሮ ምንጭ መሆናቸውን አስተምሯል፡፡

እስኪ ደግሞ የሦስተኛው ምዕተ ዓመት ጳጳስ የነበረውን የሂፖሊተስን ንግግር፣ *Against the Heresy of One Noetus* በተሰኘው ሥራው ክፍል ዘጠኝ ላይ የሰፈረውን እናድምጥ፡

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

*ወንድሞች ሆይ፣ አንድ እግዚአብሔር አለ፣ ስለ እርሱም ያወቅነው ከሌላ ከየትኛውም ምንጭ ሳይሆን ከቅዱሳት መጻሕፍት ብቻ ነው፡፡*

ቀደምቱ አብያተክርስቲያናት ጠቅላላው መጽሐፍ ቅዱስ በሐዋርያት አማካይነት ለአማኞች የተሰጡ የክርስቶስ ቃሎች መሆናቸውን ያምናሉ፡፡ በዚህም መሰረት የነገረ-መለኮት ሊቃውንቱ *sola Scriptura* ወይንም ቅዱሳት መጻሕፍት ብቻ ብለው የሚጠሩትን ጽንሰ ሃሳብ አረጋግጠውልናል፡፡ ይህም ቅዱሳት መጻሕፍት ብቸኛዎቹ የማይሻሩ የእምነት ሕግጋት እና በየትኛውም ነገረ - መለኮታዊ ሙግት የመጨረሻዎቹ ዳኞች መሆናቸውን የሚያሳየን አመለካከት ነው፡፡

የዚህንም ግልጽ ምሳሌ በ370ዓ.ም. የቂሳርያው ጳጳስ ሆኖ የተመረጠው ባሲል፣ በጻፈው ጽሑፉ ውስጥ እናገኛለን፡፡ ባሲል የቤተክርስቲያን ትውፊቶች ወይንም ልማዶች ብርቱ ተሟጋች የነበረ ሰው ሲሆን እነዚህም ትውፊቶች ከሐዋርያት ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው መሆኑን በማስረገጥ ሃሳቡን ይገልጥ ነበር፡፡ ይህም ሆኖ ግን፣ የእነዚህን ትውፊቶች እውነተኝነት አስመልክቶ ሙግት ሲነሳ፣ የመጨረሻው ሥልጣን ያለው በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ መሆኑን ያሳስብ ነበር፡፡ ለሐኪሙ ኢዩስጣጢስ በጻፈው በ189ኛው ደብዳቤው የተጻፈውን የባሲልን ቃሎች አድምጡ፡-

*እስትንፋሰ-እግዚአብሔር ያለባቸው ቅዱሳት መጻሕፍት በእኛ መሃል ይበይኑ፤ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ስምም የሆነ አስተምህሮ በተገኘበት በየትኛውም ወገን፣ እውነት ከእርሱ ጋር መሆኗ ይረጋገጥ፡፡*

በዚህ ስፍራ ባሲል አንዳንድ አብያተክርስቲያናት በእምነት ሕጋቸው ውስጥ አንዳንድ ትውፊታዊ ሃሳቦችን ሲያካትቱ፣ ሌሎቹ ደግሞ የዚያ ተቃራኒ የሆነውን የሚቀበሉ መሆኑን ዕውቅና ሰጥቷል፡፡ እንግዲያው፣ ይህንን ጉዳይ ፈር ለማስያዝ የመጨረሻው ሥልጣን ያለው በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ መሆኑን አመልክቷል፡፡

የቀደመችው ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮቶቿን በጠቅላላ በጽናት ያሳረፈችው በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ ነው፡፡ ሆኖም የቅዱሳት መጻሕፍትን አስተምህሮዎች ለመጠበቅና ጠቅለል አድርጎ ለመያዝ በትውፊታዊ አስተምህሮዎቿም ላይ ትደገፋለች፡፡

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

## ባህላዊ/ትውፊታዊ አስተምህሮዎች

እንግዲህ አሁን፣ ቤተክርስቲያን ለምን ትውፊታዊ አስተምህሮዎቿን መጠበቅ አስፈለጋት የሚለው ጥያቄ ምክንያታዊ ይሆናል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን መጠበቅና መጽሐፍ ቅዱስ ስለራሱ እንዲናገር ማድረግ አይበቃምን?

> *መጽሐፍ ቅዱስ የማያስተምረውንና ሐዋርያትም ያላስተማሩትን የሚያስተምሩ የሐሰት መምህራን በመኖራቸው ምክንያት፣ ቤተክርስቲያን የምታምንበትን አንቀጽ በአጭር እና በግልጽ አረፍተ ነገር መቅረጽ አስፈልጓል፡፡ እናም በዚህ ምክንያት፣ የሐሰት ትምህርቶችን ምላሽ ለመስጠት፣ ቤተክርስቲያን የዕምነት አንቀጾቿን በግልጽ ማጠቃለያ መንደፍ ያስፈልጋታል፡፡ (ዶ/ር ኤሪክ ኬ. ቶንስ)*

> *ቤተክርስቲያን የእምነቷ መሠረት የሆኑ ቅዱሳት መጻሕፍት በእጇ አሉ፣ ሆኖም ግን፣ ቅዱሳት መጻሕፍት ረጅም፣ እውቀት (የተማረው ወገን) ደግሞ ውሱን ነው፡፡ ስለዚህ፣ ቤተክርስቲያን ሕዝቦቿ መላውን መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብ ባይችልም እምነቱን ጥንቅቅ አድርጎ እንዲያውቅና በጽናት እንዲናገረው በሚያስችለው መጠን መሠረታዊ አስተምህሮዎቿን በአንድ የሃይማኖት መግለጫ መቅረጿ ተመራጭ ነው፡፡ (ዶ/ር ረይድ ካሲስ፣ ትርጉም)*

*በተለይ የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ የተለየ ዋጋ የሚሰጠው ነው፣ ምክንያቱም የቅዱሳት መጻሕፍት ቀኖና እስከ 397 ዓ.ም. ድረስ አልተዘጋጀም ነበርና በቀደምት የቤተክርስቲያን የታሪክ ዘመንም እንኳን አስፈላጊ ነበር፡፡ እንግዲያው ሥልጣን ያለው የቤተክርስቲያን እምነት ምንድን ነበር? በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ጠቅለል ብሎ የቀረበው ነበር፡፡ በዚያስ ዘመን ይሁን እኛ ግን መጽሐፍ ቅዱስ አለን፡፡ታዲያ፣ የሃይማኖት መግለጫው ለምን ያስፈልገናል? ምክንያቱም ሰዎች ክርስቲያን ከመሆናቸው በፊት መጽሐፍ ቅዱስን በጠቅላላ እንዲረዱ ልንጠብቅባቸው ስለማንችል፡፡ የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ አሁንም ድረስ ወሳኝ የሆኑትን የመጽሐፍ ቅዱስን አስተምህሮዎች ቀለል ባለ መንገድ ጠቅልሎ*

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

*ይዟል፡፡ በዚህም ምክንያት፣ አሁንም ቢሆን ልንጠቀምበት ይገባል፡፡ (ዶ/ር ፖል ቻንግ፣ ትርጉም)*

የስህተት አስተማሪዎች በቤተክርስቲያን ውስጥ በርካታ ችግሮችን ይፈጥራሉ፡፡ ጥቂቶቹ እንዲያውም የወንጌሉን ማዕከላዊ ሃሳብ እንኳን ይክዳሉ፡፡ እነዚህን ለመሳሰሉ ጉዳዮች ምላሽ ለመስጠት፣ እግዚአብሔርን የሚፈሩ የበሰሉ ክርስቲያኖች የቅዱሳት መጻሕፍትን ማዕከላዊ አስተምህሮዎች ጠቅለል አድርገው የሚይዙና ክርስቲያኖች በጠቅላላ የእምነትን መሠረታዊ ይዘት ሊያውቁና ሊያረጋግጡ የሚችሉባቸውን ማጠቃለያዎች ያዘጋጃሉ፡፡ ኦሪገን *On First Principles* በተሰኘው *ሥራው መቅድም* ውስጥ ሁኔታውን እንዴት እንዳስቀመጠው እስኪ አድምጡ፡-

> በርካቶች *የክርስቶስን አመለካከት እንደያዙ የሚያስቡ* አሉ፣ ከነዚህም መካከል ደግሞ ከቀደሙት አባቶቻቸው ለየት ያለ አስተሳሰብ የሚያራምዱም አሉ፣ ሆኖም ግን ከሐዋርያት ስርዓቱን ጠብቆ ሲተላላፍልን የቆየውና እስከ እኛም ዘመን ድረስ የዘለቀው የቤተክርስቲያን አስተምህሮ ብቻ ተቀባይነትን ሊያገኝ የሚገባው ሲሆን ይህም በምንም መንገድ ከቀደመው የቤተክርስቲያን አስተምህሮና ከሐዋርያት ትውፊት የተለየ እውነት ይዞ ሲገኝ ከበሬታ ሊቸረው አይገባም፡፡

በዚህ ስፍራ ኦሪገን ምን እንደተናገረ ልብ በሉ፡፡ የቤተክርስቲያን አስተምህሮ የማይሻር፣ ወይንም ዘወትር ምንም እንከን የማይገኝበት ነው አላለም፡፡ የቤተክርስቲያን አስተምህሮ እውነተኛ እንደሆነ ተቀባይነትን ሊያገኝ የሚገባው ወይም ተቀባይነትን የሚያገኝበት ምክንያት ከሐዋርያት ስርዓቱን ጠብቆ እስከ እርሱ ዘመን ድረስ በትክክል በመተላለፉ ነው ያለው፡፡ በሌላ አባባል፣ በኦሪገን ዘመን የቤተክርስቲያን አስተምህሮ፣ በቅዱሳት መጻሕት ከሰፈሩት የክርስቶስ ቃላት ጋር ስምም የሆኑ ማጠቃለያዎች ነበሩ ማለት ነው፡፡ በዚህም ምክንያት፣ በእርሱ ዘመን የነበረችው ቤተክርስቲያን እነዚያን ማጠቃለያዎች አስተምህሮዎችን የሚመረምሩባቸው "ልኬቶች" ወይም "የእምነት አንቀጾች" አድርገው መጠቀም ችለው ነበር፡፡ ሆኖም የመደምደሚያው ሥልጣን የሚያርፈው ግን በአዲስ ኪዳን ላይ እንጂ በዘመነኛዋ ቤተክርስቲያን ላይ አይደለም፡፡

ምናልባት ይህንን ሃሳብ በበርካታ የመተሳሰሪያ ቀለበቶች የተሠራውን ሰንሰለት በማሰብ ብናብራራው የተሻለ ይሆናል፡፡ የቀደመችው ቤተክርስቲያን በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ተጽፈው የሚገኙ የክርስቶስ ትምህርቶችን በጽናት መጠበቅ ትፈልግ ነበር፡፡ ይህም ክርስቶስን የመጀመሪያው የትስስር ቀለበት ያደርገዋል፡፡ ሐዋርያት ደግሞ ከክርስቶስ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ነበራቸው፣ በቀጥታም ከእርሱ ተማሩ፡፡ እናም፣ የእነርሱ ትምህርቶች የሰንሰለቱ ሁለተኛ ቀለበት ሆኑ ማለት ነው፡፡ ሐዋርያትም ስለ ክርስቶስ የነበራቸው እውቀት በቅዱሳት መጻሕፍት ተጠብቆ እንዲቆይ በማድረግ ቅዱሳት መጻሕፍት የሰንሰለቱ ሦስተኛ ቀለበት እንዲሆን አደረጉ፡፡ እነዚህ ሦስቱ ቀለበቶች ፍጹምና የማይሻሩ ነበሩ ምክንያቱም በመንፈስ ቅዱስ ሉዓላዊ ፈቃድ አስቀድመው የታቀዱ ነበሩና፡፡

ነገር ግን አራተኛውና የቤተክርስቲያንን ትውፊታዊ ትምህርቶች የያዘው ቀለበት ልዩነት አለው፡፡ እነዚህ ትምህርቶች ከትውልድ ወደ ትውልድ የተላለፉባቸው መንገዶች የማይሻሩ አልነበሩም፤ ያለ አንዳች ስህተት ስለመጠበቃቸውም መንፈስ ቅዱስ ዋስትና አይሰጠንም፡፡ እንዲያውም፣ ቀደም ብለን እንደተመለከትነው፣ የአንዳንድ አብያተክርስቲያናት ልምዶች ከሌሎቹ ጋር የሚቃረን ነው፡፡

ከእነዚህም ትምህርቶች መካከል አንዳንዶቹ፣ ቅዱሳት መጻሕፍት በቀጥታ በማያስቀምጡዋቸው፣ ጥቃቅን ልምምዶች ላይ ይመሰረታሉ፡፡ አንዳንዶቹ ትውፊታዊ አስተምህሮዎች ግን፣ በተለይም ዋነኛ ከሆኑት የእምነት አንቀጾች አንፃር፣ በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ እንደተዘረዘሩት ዓይነቶቹ የቅዱሳት መጻሕፍትን ትክክለኛ ትርጉም ጠቅለል አድርገው ያቀርቡልናል፡፡

ወደ እነዚህ ማዕከላዊ የእምነት አንቀጾች ስንመጣ፣ ትውፊቶቹ በየዘመናቱ በተነሱ የቤተክርስቲያን መሪዎች ይሁንታን አግኝተዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ፣ ከቅዱሳት መጻሕፍት በቀጥታ በሚያቀርቡዋቸው ማጣቀሻዎች ትክክለኝነታቸው የተረጋገጠ ሆኗል፡፡ አሪገን ትውፊታዊው የቤተክርስቲያን አስተምህሮ የቤተክርስቲያን የእምነት አንቀጽ እንዲሆን ያለማመንታት ያስቀመጠው በዚህ ምክንያት ነው፡፡

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

ሆኖም ግን፣ ይህኛው ቀለበት የማይሻር አይደለም፡፡ አብያተክርስቲያናት፣ የምክክር ጉባዔዎቻቸው እና ግለሰብ ክርስቲያኖች፣ ስህተት ሊፈጽሙ ይችላሉ፡፡ በሦስተኛው ምዕተ ዓመት ይኖር የነበረው የከርቴጁ ጳጳስ ሳይፕሪያን፣ በጻፈው በ73ኛው ደብዳቤው ላይ የሮማውን ጳጳስ የእስጢፋኖስን አስተምህሮዎች በመቃወም የጻፈውን እስኪ አድምጡ፡-

*አንዳንዶች እውነት ተጠብቆ እንዳይቆይና ድል ነሺ እንዳይሆን የሚከላከሉ ሰዎች በስውር እንደሚያደቡት፣ ልማድ ያለ እውነት ዘመን ያስቆጠረ የስህተት ቋት ነው፡፡*

የሳይፕሪያን ነጥብ የአንዳንድ ቀደምት ክርስቲያኖች አተያይና እና ልምምዶች ከሐዋርያት በተላለፉልን እውነቶች ላይ ስራቸውን የሰደዱ አይደሉም የሚል ነው፡፡ በፈንታው፣ "ዕድሜ ጠገብ የስህተት ቋቶች" ናቸው፡፡ ስህተቶቹም ዘመናትን እያስቆጠሩ በቤተክርስቲያን ውስጥ አድብተው ተቀምጠዋል፡፡ እንዲያውም፣ ቤተክርስቲያን የእምነትን አንቀጾች በትክክል በጽሑፍ በማስፈር ማቆየት እንዲገባት የሚያስገድዳት ምክንያት ይኸው የሰው ተለዋዋጭነት ነው፡፡ አሪገንና ቀደምት የሆኑት የቤተክርስቲያን አባቶችም የእምነትን አንቀጾች ጽፈው ያስቀመጡት በመላው ዓለም የሚኖሩ ክርስቲያኖች አስተምህሮዎቻቸውን ከትውፊቶቹ ጋር በማስተያየት ትክክለኛውን እንዲለዩት ለማገዝ ነው፡፡ የአብያተ ክርስቲያናት የምክክር ጉባዔዎችም ትውፊታዊ አስተምህሮዎቻቸውን በጽሁፍ በማስቀመጥ በተለያየ ስፍራና ቦታ የሚገኙ ክርስቲያኖች እውነቱን እንዲያውቁ ያደርጋሉ፡፡

በሁሉም መንገድ፣ የቤተክርስቲያንን ትውፊታዊ አስተምህሮዎች ጠብቆ የማቆየቱ ግብ አብያተክርስቲያናት የቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረታዊ ትርጉም እንዳያጣርሱ፣ አማኞች የሐዋርያትን ትምህቶች በትክክል እንዲረዱ፣ ያለማወላወልም እንዲጨብጧቸውና በክርስቶስ ቃሎች መሠረት እንዲኖሩ ለማድረግ ነው፡፡

*መጽሐፍ ቅዱስ በጣም ትልቅ መጽሐፍ ነው፣ እናም ስለራሱ በአንዲት ዐረፍተ ነገር እንዲናገር መጠበቅ የለባችሁም፣ መልካም የሆነ ማጠቃለያ ልትሰጡበት ይገባል፡፡ በአዲስ ኪዳን ዘመን እንኳን በክርስቶስ ማንነት አስተምህሮዎች ላይ ዋና ተግዳሮቶች ነበሩ፡፡ ሐዋርያት "አይደለም፣ እውነቱ ይህ ነው" በማለት ሲሟገቱ የምትመለከቱዋቸው ለዚህ ነው፡፡ እነዚሁ በክርስቶስ ማንነት አስተምህሮዎችና በመጽሐፍ ቅዱስ ማንነት ላይ የነበሩ ዋና ተግዳሮቶች እስከ ሁለተኛው ዓመተ ምህረት ድረስም ዘልቀው ነበር፡፡ ስለዚህም በተቻላቸው መጠን ሁሉ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊውን የእምነት መግለጫ አጭርና በዋናው ነጥብ ላይ ባተኮረ መንገድ ጠቅለል አድርገው ማቅረብ ነበረባቸው፡፡ ለሐዋርያት የእምነት*

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

*መግለጫ ልደት ምክንያት የሆነው ይኸው ነው፡፡ ልብ ልንለው የሚገባ አስፈላጊ ነገር፣ እነርሱ የሞከሩት በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ለመጨመር ሳይሆን፣ ፍቺውን አብራርተው ለማቅረብ የሞከሩ መሆኑን ነው ፡፡ (ዶ/ር ፒተር ዎከር)*

ባሲል በ374 ዓ.ም. *On the Holy Spirit በተሰኘው ጽሁፉ እንዳሰፈረው፡*

*አባቶቻችን የተናገሩትን፣ እኛም እንናገራለን … ሆኖም ግን የአባቶቻችን ትውፊት በመሆኑ ላይ ብቻ አንደገፍም፤ የቅዱሳት መጻሕፍትን እውነት በማንገባቸውም እንጂ፡፡*

ትውፊታዊ ትምህርቶቿን ከመከላከል አንፃር፣ የቀደመችው ቤተክርስቲያን ስለጥቃቅን አስምሮታዊ ነጥቦች እምብዛም አትጨነቅ እንደነበረ መግለጽ ይገባናል፡፡ በማዕከላዊዎቹና ለድርድር በማይቀርቡት መሠረታዊ እምነቶችና ልምምዶች ላይ ትኩረት ያደርጉ ነበር፡፡ ይህንንም በሚያነሷቸው የመከራከሪያ ሃሳቦች እና በጽሑፍ ባሰፈሯቸው የእምነት አንቀጾቻቸው ዝርዝር ውስጥ ጥርት አድርገን እንመለከተዋለን፡፡

ለምሳሌ፣ የክርስቶስን ሰብዕና የሚክዱትን ዶሴታውያን በመቃወም ጽፈዋል፡፡ የብሉይ ኪዳኑ አምላክ፣ የተለያዩ ሥጋዊ ኃጢአቶች እንዲፈፀሙ የፈቀደ ክፉ ነው፣ ብለው የሚምኑትን ኖስትሳውያን በመቃወምም ጽፈዋል፡፡ የቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረታዊ የእምነት አውታሮች የሚፈታተኑ በርካታ የስህተት ትምህርቶችንም በመቃወም ጽፈዋል፡፡

ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት እና ስለ ቤተክርስቲያን ትውፊታዊ ትምህርቶች በመነጋገር፣ የሐዋርያት የእምነት መግለጫ የቤተክርስቲያንን ትውፊታዊ አስምህሮዎች ጠቅለል አድርጎ እንዴት እንደያዘ ለእያንዳንዱ አማኝ ጠቀሜታ ስንል እንመለከታለን፡፡

# የሐዋርያት የእምነት መግለጫ

ቀደም ብለን እንደተመለከትነው፣ የሐዋርያት የእምነት መግለጫ በስፋት አገልግሎት ሲሰጥበት የቆየው አዳዲስ አማኞች መሠረታዊ የሆኑትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርቶች በትክክል ማመናቸውን ለማረጋገጥ ነው፡፡ የዘመናችን አብያተክርስቲያናት አዳዲስ አማኞችን በክፍል ውስጥ እና በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች ደቀመዛሙርት እንደሚያደርጉት ዓይነት የቀደመችውም ቤተክርስቲያን ለአዳዲስ አማኞች መሠረታዊ የእምነት አንቀጾችን ለማስተማር የእምነት መግለጫዎችን ትጠቀም ነበር፡፡

ከክርስቶስ ልደት በኋላ ከ354 – 430 ዓ.ም. ባለው ዘመን የኖረው የሂፖው እውቅ ጳጳስ አውጉስቲን፣ ለጥምቀት ሥርዓት ለተዘጋጁ አዳዲስ አማኞች ባቀረበው መልእክት ላይ፣ የእምነት

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

መግለጫዎችን ዋጋ ጠቅለል አድርጎ አቅርቧል፡፡ በዚህ ስብከት ላይ፣ እርሱ በአዕምሮው ይዞት የነበረው የኒቂያውን የእምነት መግለጫ ሲሆን፣ ንግግሮቹ ግን በመጀመሪያዎቹ ምዕተ ዓመታት የነበረችው ቤተክርስቲያን ትጠቀምባቸው የነበሩትን የእምነት መግለጫዎች ዓላማና አጠቃቀም በትክክል አጠቃልለው ያቀረቡ ነበሩ፡፡ *A Sermon to the Catechumens በተሰኘውና በሃይማኖት መግለጫ ላይ ባቀረበው መልእክት አውጉስቲን ይህንን ጽፏል፡-*

> *አሁን ያደመጣችኋቸው እነዚህ ቃላት በመለኮታውያኑ ቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ወደ ታችና ወደላይ ተበታትነው የሰፈሩ፣ ከያሉበት ተሰብስበውና ተመጥነው በአንድነት የተቀመጡ፣ የማስታወስ አቅሙ አነስተኛ የሆነ ሰው ሳይጨናነቅ፣ እያንዳንዱ ሰው የሚያምነውን እንዲናገርና አጥብቆ እንዲይዝ የሚያስችሉት ናቸው፡፡*

በዚህ ስፍራ አውጉስቲን እንደጠቀሰው፣ የክርስትና መሠረታዊ ትምህርቶች በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ እዚህም እዚያም ተበታትነው ተቀምጠዋል፡፡ ስለዚህም፣ የጥንቶቹ አብያተክርስቲያናት የቅዱሳት መጻሕፍትን ዋነኛ አስተምህሮዎች በሃይማኖት መግለጫዎች ጠቅለል አድርገው አስቀምጠዋቸዋል፡፡ ይህም እያንዳንዱ አማኝ  አውጉስቲንም እንዳስቀመጠው "ዝቅተኛው" ወይንም ያልተማረው እንኳን መሠረታውያኑን የቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርቶች ማረጋገጥና አጽንቶ መያዝ እንዲችል ያደርገዋል፡፡

እርግጥ ነው፣ የተለያዩ ቤተ እምነቶች የተለያዩ የሃይማኖት መግለጫዎች እንዳሏቸው ሁሉ፣ የተለያዩ የእምነት መመዘኛዎች ይኖሯቸዋል፡፡ አንዳንዶቹ አብያተክርስቲያናት ከአዳዲስ አማኞች ድርሻ አንጻር በቂ መረዳቶችን ካላካተተ አንቀበልም የሚል አቋም የሌላቸው ሲሆን፣ ሌሎቹ ደግሞ እውነተኛ እምነት ኖሮት ጠለቅ ያለ ነገረ-መለኮታዊ እውቀት ከሌለው አይቀበሉትም፡፡ በውጤቱም፣ አንድ ሰው በአንዱ ቤተ ክርስቲያን እንደ አማኝ ሲቆጠር በሌላው ግን አይቆጠርም ማለት ነው፡፡  በዚህም መለያየት ምክንያት፣ የቀደመችው ቤተክርስቲያን ራሳቸውን ክርስቲያን ብለው በሚጠሩ ቤተ እምነቶች ሁሉ ተቀባይነት የሚኖረውን የሃይማኖት መግለጫ ማውጣት አስፈላጊ መሆኑን እውቅና ሰጠች፡፡

ይህንንም መሻት ለማሟላት የሐዋርያት የእምነት መግለጫ ቀደምቱን ስፍራ ይዞ ወጣ፡፡ አጭር፣ የእምነት አንቀጾችን በቀጥታ የሚያስቀምጥ እና ክርስቲያን ነኝ የሚል ሁሉ ሊረዳው የሚገባ ነው፡፡

> *የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ የክርስትና እምነት ትረካዊ ማጠቃለያ ነው፡፡ ምንም እንኳን እያንዳንዷ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል የማይሻርና እንከን የለሽ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን ብናምንም፣ ሰዎች የወንጌልን መሠረታዊ ጭብጥ በቀላሉ እንዲረዱት የሚያስችል ማጠቃለያ መስጠት አስፈላጊ መሆኑንም ያመለክተናል፡፡ የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ያን የሚመስል ማጠቃለያ ነው፡፡ የእምነትን ፍሬ ነገር አስመልክቶ ሐዋርያት ከጌታ በተቀበሉት*

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

*መገለጥ ላይ ተመሥርተው ምን እንዳስተማሩ ፈልቀቅ አድርጎ የሚያሳየን ገና በክርስትና ትውፊት የመጀመሪያ ዓመታት ላይ ብቅ ያለ ነው፡፡ “አምናለሁ፡፡” ሁሉም ነገር የሚመነጨው ከዚህ ውስጥ ነው፡፡ እናም፣ በዚህ ስፍራ ዋናው አስፈላጊ ነገር የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ወንጌልን ልናስተላልፈው በሚገባ መጠን እናስተላልፈው ዘንድ ማለት የሚገባንን ሳናዛንፍ እንድንል ይረዳናል፡፡ (ዶ/ር ዳግማዊ አር. አልበርት ሞለር)*

እንግዲህ ስለ ሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ታሪክ ይህንን ካልን፣ መግለጫው የሚሰጣቸውን ማረጋገጫዎች በወፍ በረር እንዳስሳለን፡፡ የክርስቲያኖች እምነት ትልቁን ምስል መረዳት በቀደምቷ ቤተ ክርስቲያን አስፈላጊ የሆነውን ያህል በዛሬውም ዘመን እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡

# 3. ወፍ በረር ዳሰሳ

ለበርካታ ዓመታት ያህል፣ የነገረ-መለኮት ምሁራኑ የሐዋርያትን የሃይማኖት መግለጫ ይዘቶች በተለያዩ መንገዶች ገልጠዋቸዋል፡፡ በዚህ ትምህርት፣ የሐይማኖት መግለጫውን የእምነት አንቀጾች ከሦስት አመለካከት አንጻር እንዳስሰዋለን፡፡ በመጀመሪያ፣ ስለ ትምህርተ እግዚአብሔር ዳሰሳ እናደርጋለን፡፡ ሁለተኛ፣ ስለ ቤተክርስቲያን እንነጋገራለን፡፡ ሦስተኛ ደግሞ፣ ስለ ድነት እንነጋገራለን፡፡ በመጀመሪያ በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ውስጥ የተጠቀሰውን ትምህርተ እግዚአብሔርን እንመልከት፡፡

## እግዚአብሔር

*ትምህርተ እግዚአብሔር ክርስቲያናዊ ነገረ-መለኮትን፣ ክርስቲያናዊ እምነትን እና ክርስቲያናዊ ልምምዶቻችንን አስመልክቶ ለምንናገረው ነገር ሁሉ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ ራሳችንን፣ ዓለምን፣ የመኖራችንን ትርጉምና ዓላማ እንዴት እንደምንረዳ አተያያችን በጠቅላላ የተሳሰረው ከእግዚአብሔር ማንነት ጋር ነው፡፡ እያንዳንዷ ክርስቲያናዊ አስተምህሮ ስለ ድነት ቢሆን፣ ስለ ቤተክርስቲያን ቢሆን፣ የወደፊቱን አስመልክቶ ስለ መጨረሻው ዘመን ቢሆን፣ ሁሉም የተመሠረተው ዘላለም በሚኖረው በስላሴ ላይ ነው፡፡ በዚህ በምድር ሕይወታችን ተስፋና መተማመኛችን፣ ስለ መዳናችንና ለኀጢአታችን ስለ ተቀበልነው ስርየት ያሉት ነገሮች ሁሉ የሚያያዙት፣ ሁሉን ካቀደው፣ ፈቃዱንና ዓላማውን ከሚገልጠውና ያለ ከልካይ ሁሉንም ከሚፈጽመው እግዚአብሔር ጋር የተሳሰረ ነው፡፡ ስለዚህ ሁሉም ነገር የሚያጠነጥነው ስለ እግዚአብሔር ባለን መረዳት ላይ ነው፡፡ (ዶ/ር ስቴፈን ዌሉም)*

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ላይ ሰፍረው የምናገኛቸው የትምህርተ እግዚአብሔር ሁለት ዋነኛ መግለጫዎች አሉ፡፡ በመጀመሪያ፣ የሃይማኖት መግለጫው እግዚአብሔር በስላሴነት የሚኖር በመሆኑ ላይ የተዋቀረ መሆኑ ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ፣ እግዚአብሔር አብ፣ እግዚአብሔር ወልድና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ተብለው ስለሚጠሩት የእግዚአብሔር ሰብእና መግለጫዎች ይሰጠናል፡፡ በመጀመሪያ ስላሴን እንመልከት፡፡

## ስላሴ

የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ እያንዳንዳቸው "እኔ … አምናለሁ" የሚል መግቢያና ማሰሪያ ባላቸው ሦስት ዋና ክፍሎች የተከፈለ መሆኑን አስተውላችኋል፡፡ የመጀመሪያው ክፍል በእግዚአብሔር አብ ስለማመን ይናገራል፡፡ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ በአንድያ ልጁ፣ በጌታችን በኢየሱስ ስለማመን ይናገራል፡፡ ሦስተኛው ክፍል ደግሞ፣በመንፈስ ቅዱስ ስለማመንና ስለ እርሱ አገልግሎቶች ይዘረዝራል፡፡

በዚህ ስፍራ ግን፣ ሁሉም የጥንት የሃይማኖት መግለጫ ቅጂዎች ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ በተጻፉት አንቀጾች ላይ "እኔ … አምናለሁ" የሚሉትን ቃላት የማያስቀምጡ መሆኑን ማመልከት ይገባናል፡፡ በእነርሱ ምትክ፣ አብዛኞቹ "እና፣" የሚለውን ቃል የሚጠቀሙ ሲሆን በዚህም አውድ መሠረት ይህ ቃል "እኔ … አምናለሁ" ከሚለው ጋር እኩል ኃይል ያለው ነው፡፡ ሆኖም ግን በሁሉም ቢሆን፣ የእግዚአብሔርን ማንነት አስመልክቶ የሃይማኖት መግለጫው ክፍሎች በዓለም አቀፍ ደረጃ በቤተክርስቲያን ተቀባይነትን ያገኘ ነው፡፡ ይህ ቀመር ስላሴአዊነት ነው፡፡ ያም፣ አንድ አምላክ አለ፣ እርሱም በሦስት ማንነቶች ይኖራል፣ እነርሱም እግዚአብሔር አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡

ይህም ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ በሰጠው ተልዕኮ በማቴዎስ 28፥19 ተመዝግቦ ከምናገኘው ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡

> እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው (ማቴ 28፥19)

በዚህ ስፍራ፣ ልክ በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ላይ እንደተቀመጠው ዓይነት፣ ሦስቱ ስሞች በእኩያ አገላለጥ በአንድነት መቀመጣቸው አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የራሳቸው ሰብእና ያላቸው አንድ አምላክ መሆኑን ያሳያል፡፡

የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ "ስላሴ" የሚለውን ቃል ለይቶ የማያስቀምጥ፣ ወይም ዝርዝርም የማይሰጥ መሆኑን እንቀበላለን፡፡ ነገር ግን የሃይማኖት መግለጫው የተመጠነ የእምነት መግለጫ

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

እንጂ ዝርዝር የእምነት አንቀጽ አለመሆኑን ማስታወስ ይገባል፡፡ ከዚያም በቤተክርስቲያን ስርዓት ውስጥ አገልግሎት ላይ ሲውል፣ እነዚህን የእግዚአብሔር ሦስት ስብእናዎች በዚህ መንገድ መግለጡ የስላሴን ጽንሰ ሃሳብ እንደሚያነግብ በቤተክርስቲያን የሚገኝ ሰው ሁሉ ያውቃል፡፡

እንግዲህ አሁን፣ ሁሉም ክርስቲያን ስላሴ የሚለውን ቃል ፍቺ ሙሉ በሙሉ ሊረዳ ስለማይችል፣ ብዙ ማብራሪያ ለመስጠት ከመሞከር መታቀብ ይገባናል፡፡ ስላሴ በአብዛኛው (በተለምዶ) እንዲህ ይገለጣል፡

እግዚአብሔር አንድም ነው ሦስትም ነው፡፡

አንድ ነው ስንል መሠረታዊ ማንነቱን ማመልከታችን ሲሆን፣ ሦስት ነው ስንል ግን ራሳቸውን የቻሉ ማንነቶች ማለታችን ነው፡፡

እርግጥ ነው፣ የስላሴን ጽንሰ ሃሳብ በሰብዓዊ አዕምሮ ሙሉ በሙሉ መረዳት አዳጋች ነው፡፡ ምንም አንኳን፣ ስላሴ ክርስትና ከሚለይባቸው የእምነት አቋሞቹ ተቀዳሚና ዋነኛው ቢሆንም፣ የእግዚአብሔር ኅላዌና ማንነት ከእኛ የልምምድ አድማስ እጅግ ሩቅ ስለሆነ እኛ ሙሉ ለሙሉ ልንረዳው አንችልም፡፡ ግን እስኪ አንድ ጥያቄ እንጠይቅ ይህንን የመሰለው ውስብስብ አስተምህሮ በክርስቲያናዊ ነገረ መለኮት ውስጥ ወሳኝ የማዕዘን ድንጋይ እንዴት ሊሆን ቻለ?

*ስላሴ፣ መጽሐፍ ቅዱስን በተቀደሰ መንገድ በምታነብበት ወቅት የምትረዳው ነገር ነው፡፡ አብ አምላክ እንደሆነ፣ ወልድ አምላክ እንደሆነ እና መንፈስ ቅዱስ አምላክ እንደሆነ ሁሉም የየራሳቸውን ማንነት ይዘው በግልጽ ትመለከታለህ፡፡ እናም ስለዚህ የቅዱሳት መጻሕፍትን ትምህርት ከትምህርተ ስላሴ ጋር ማጣጣሙ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ [ዶ/ር ኤሪክ ኬ.ቲዮኔስ]*

*እንግዲያው ትምህርተ ስላሴ ለክርስቲያናዊ ነገረ መለኮት የማዕዘን ድንጋይ ከሆነ፣ ከሁሉ አስቀድሜ ልረዳው ያስፈልገኛል ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ ነውና፡፡ ጽንሰ ሃሳቡ እንጂ ስ-ላ-ሴ የሚለው ቃል ፊደል በፊደል ተቀምጦ ስላማናገኘው እንዴት እንደምንረዳው መጠንቀቅ ይገባናል፡፡ እንግዲያው ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ እግዚአብሔር ማንነት የሚያስተምሩን ድምር ትምህርት እንደሚነግረን እግዚአብሔር አንድ ነው፣ ይህም አብ አምላክ ነው፣ ወልድ አምላክ ነው፣ መንፈስ ቅዱስም አምላክ ነው- በአንድነትም፣ በጠቅላላው የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ስንገልጠው እግዚአብሔር ስሉስ ቅዱስ ነው የሚለውን ድምዳሜ እንድንሰጥ ዋስትና ይሰጠናል፡፡ [ዶ/ር ሮበርት ጂ. ሊሰር]*

እንግዲያው፣ እግዚአብሔር አንድ ነው ስንል፣ እግዚአብሔር አንድ አምላክ ነው የሚለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት እያረጋገጥን (እየተሟገትንለት) ነው ማለት ነው፡፡ እናም እነዚህ ሦስት ኑባሬዎች እንዴት አንድ አምላክ እንደሆኑም ለማብራራት መሞከራችን ነው፡፡ ማንነት ወይንም ኑባሬ የሚለውን ቃል ስንጠቀም ሦስቱም ኅላዌ መለኮት የሚጋሩት እንድነት እንዳላቸው

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

እያመለከትን ነው፡፡ ማለትም በእግዚአብሔር አብ ውስጥ ያለው እንደዚያው በወልድ ውስጥ አለ እንደዚያውም በመንፈስ ቅዱስ ውስጥም አለ ማለት ነው፡፡

እግዚአብሔር በሦስትነትም ይኖራል ስንል፣ አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የራሳቸው መለያ አላቸው የሚለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት እየተሟገትንለት ነው፡፡ በራሳቸው ኅላዌ ያላቸው አንዳቸው ከሌላቸው ጋር የሚዋሃዱ፣ አንዳቸው ከሌላቸው ጋር የሚጣጣሙ፣በቅርብ ግንኙነትም የተሳሰሩ ናቸው፡፡

በብዙ መንገዶች፣ የስላሴ ጽንሰ ሃሳብ ትልቅ ምስጢር ነው፡፡ ግን ደግሞ ስለ ልዕለተፈጥሮአዊው አምላካችን የተሰጡትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርቶች ሳያዛንፍ ጠቅለል አድርጎ የያዘም ነው፡፡

የስላሴ ነገር ለክርስቲያናዊ ነገረ መለኮት ወሳኝ የሚሆነው በብዙ ምክንያት ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል፣ ኢየሱስ አምላክ መሆኑን ያረጋግጣል፣ በተጨማሪም ኢየሱስ እግዚአብሔር እራሱን በስውር የገለጠበት ብቻ ማለትም አይደለም፡፡ የአንድ አምላክ አማኞች ለምን እንደሆንንም ያብራራል፣ ምንም እንኳን ሦስቱን ስላሴ አብን፣ ወልድንና መንፈስ ቅዱስን ብናመልክና ወደ እነርሱ ብንጸልይም *አንዱን ብቻኛ አምላክ እናመልካለን፡፡ ከዚህም ባሻገር፣ ለሦስቱም የስላሴ አካላት ተገቢ ክብር እንድንሰጥ ያስችለናል፡፡ በተጨማሪም ከሦስቱ ስላሴዎች የአንዱ ኅልውናና ረድኤት የራሱ የእግዚአብሔር እንደሆነ እንድናውቅም ይሞግተናል፡፡ በመሠረቱ፣ የስላሴ እምነት ለበርካታ ክርስቲያናዊ ሃሳቦች መሠረታዊና ታሪካዊ ክርስትናን ያለ እርሱ ማሰብ አዳጋች ነው፡፡*

*ከስላሴ አንጻር በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ የተቀመጠውን ትምህርተ እግዚአብሔርን ከተመለከትን፣ አንዳቸው ከሌላቸው ተለይተው የሚታወቁበት የራሳቸው ማንነት ያላቸውን የስላሴ አካላትን አስመልክቶ ያስቀመጠውን ሃሳብ ለመገንዘብ ዝግጁ ነን ማለት ነው፡፡*

**ማንነት**

ከአብ አንጻር፣ የሃይማኖት መግለጫው የሁሉን ቻይነትን የባሕርይ መገለጫ ይሰጠዋል፣ የሰማይና የምድር ፈጣሪነትንም ታሪካዊ ጭብጥ ይገልጣል፡፡ እግዚአብሔር ከሉዓላዊነቱና ከማይገደበው ኃይሉ እጅግ የሚልቅ የባሕርይ መገለጫ አለው፣ ፍጥረተ ዓለምንም ከመፍጠርም የዘለለ ዕፁብ ድንቅ ተግባር አለው፡፡ በሃይማኖት መግለጫው ላይ ስለ አብ የተቀመጠው መግለጫ በሉዓላዊና መለኮታዊ አምላክ እንደሚያምኑ ከሚገልጹ ሌሎች እምነቶች ክርስትናን ለየት በሚያደርግ መንገድ አላስቀመጠውም፡፡ ነገር ግን የቀደመችው ቤተክርስቲያን እነዚህ መግለጫዎች አንድ ሰው ስለ አብ ሊኖረው የሚገባውን እምነት አስመልክቶ ለመግለጥ የሚያስችሉት ብቁና ከክርስትና ጋር የሚጣጣሙ ናቸው በማለት አረጋግጣለች፡፡ እናም ክርስትናን በዙሪያው ካሉት ሃይማኖቶች ለመለየት በሃይማኖት መግለጫው በሌላ አንቀጽ ማስቀመጥን መርጠዋል፡፡

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

ለመጥቀስ ያህል፣ የሃይማኖት መግለጫው ስለ ወልድ፣ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ብዙ ይናገራል፡፡ ምንም እንኳን ከእርሱ የባህርይ መገለጫዎች አንዳቸውንም ባይጠቅስም፣ ስለ ምድራዊ ሕይወቱና አገልግሎቱ ብዙ ዝርዝሮችን ጠቅሷል፡፡ እነዚያም ከቤተክርስቲያን ውጪ ባሉቱ ዘንድ የሚካዱ ናቸው፡፡

የሃይማኖት መግለጫው፣ ስለ ኢየሱስ ትስጉት፣ እንደ ሰብዓዊ ሕፃን ወደ ምድር ስለመምጣቱ፣ እንደ ፍፁም ሰው ስለ መኖሩ ያወሳል፡፡ በተጨማሪም ስለ መከራው፣ ስለ ሞቱ፣ ስለ መቀበሩ፣ ስለ ትንሣኤው እና ወደ ሰማይ ስለ ማረጉ ይናገራል፡፡ እነዚህ መሠረታዊ እውነታዎች ከተከናወኑበት ጊዜ አንስቶ የማያምኑ ሰዎች ይከዱዋቸው እንደነበሩ ቅዱሳት መጻሕፍት ይነግሩናል፡፡

በዛሬውም ዘመን እንኳን፣ ለዘብተኛ የታሪክ እና የነገረ-መለኮት ምሁራን፣ በርካታ ክርስቲያናዊ የስህተት አስተምህሮዎችና የተሳሳቱ ሃይማኖቶች እንደሚያደርጉት ሁሉ እነዚህን እውነታዎች ይክዳሉ፡፡ ለምሳሌ፣ እስልምና ኢየሱስ የእግዚአብሔር እውነተኛ ነቢይ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ ሆኖም ግን እርሱ ፈጽሞ አልተሰቀለም ወይም ከሞት አልተነሣም ይላል ደግሞም መለኮትነቱንም ይክዳል፡፡

በመጨረሻም የሃይማኖት መግለጫው በመጨረሻው ቀን ኢየሱስ በሰው ዘር ሁሉ ላይ እንደሚፈርድ፣ ከፉዎችንም እንደሚኮንናቸው፣ አማኞችን ግን ዘላለማዊ የተባረከ ሕይወት እንደሚሰጣቸው ይገልፃል፡፡

የሃይማኖት መግለጫው፣ ስለ መንፈስ ቅዱስም ድንግል ማርያም ኢየሱስን እንድትፀንስ ማድረጉን ይናገራል፡፡ ከዚያም ሌላ፣ ከስላሴ አንዱ መሆኑን በስሱ ገለጥ ያደርጋል፡፡ ሆኖም ግን፣ ለየት ባለ መንገድ፣ የሃይማኖት መግለጫው መንፈስ ቅዱስን ከቤተክርስቲያን ጋር ያቆራኘውና እኛም አሁንና ወደፊት ከምንለማመደው ድነት ጋር ያገናኘዋል፡፡

ስለ እያንዳንዳቸው የስላሴ አካላት ወደፊት ብዙ የምንለው አለን፡፡ ለአሁኑ ግን የሃይማኖት መግለጫው ትኩረት ያደረገው ስላሴያዊነትን በማረጋገጡ ላይ ብቻ ሳይሆን፣ እያንዳንዳቸው የስላሴ አካላት ከክርስቲያናዊ እምነት ጋር ስላላቸው ግንኙነትም ጭምር መሆኑን መግለጥ እንወዳለን፡፡ ምንም እንኳን አንቀፆቹ ዝርዝር ባይሆኑም የሃይማኖት መግለጫው ታሪካዊ ክርስትናን የሚቀበሉት ከማይቀበሉት የሚለዩባቸውን በቂ መረጃዎች ስለ እግዚአብሔርና ስለ አካላቱ ይሰጣል፡፡

እስካሁን ድረስ ስለ እግዚአብሔር የተጻፉትን አስተምህሮዎች ገልጠናል፣ አሁን ደግሞ የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ስለ ቤተ ክርስቲያን የሚናገረውን ለማመልከት ተዘጋጅተናል፡፡

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

# ቤተ ክርስቲያን

የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ቤተክርስቲያንን በሁለት የተለያዩ ሐረጎች ይገልጣታል፡፡ መጀመሪያ፣ ቤተክርስቲያን ቅድስት ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ተብላ ተጠርታለች፡፡ ሁለተኛ፣ ቤተክርስቲያን የቅዱሳን አንድነት ተብላ ተገልጣለች፡፡ እነዚህ ሐረጎች በበርካታ መንገዶች ሊተረጎሙ ይችላሉ እናም ወደፊት ባሉት ትምህርቶች ሰፋ ባለ ጥልቀት እንመለከታቸዋለን፡፡

ለአሁኑ ግን፣ ቅድስት ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን የሚለው ሐረግ የሮማዋን ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የሚያመለክት ሳይሆን በመላው ዓለም የምትገኘውን ቤተክርስቲያንና በውስጧ የሚገኙ አካሎቿን የሚያያሳይ መሆኑን ማመልከት እንወዳለን፡፡

ምንም እንኳን ለአብዛኞቹ የፕሮቴስታንት አማኞች በየትኛው ቅርጽ በቤተክርስቲያን ማመን የሚለው ቃል እንግዳ ቢሆንባቸውም፣ የሃይማኖት መግለጫው “በቤተክርስቲያን አምናለሁ” የሚለውን ሐረግ ሲያስቀምጥ እምነታችንን በቤተክርስቲያን ላይ እናደርጋለን ማለት እንዳልሆነ ይልቁኑም፣ ቤተ ክርስቲያን ቅድስት ወይም የተቀደሰች ደግሞም ካቶሊካዊት ማለትም ዓለምአቀፋዊት መሆኗን ማመልከቱ መሆኑን መግለጥ ይጠቅማል፡፡

እናም የቅዱሳን አንድነት ይህም የአማኞች ኅብረት መኖሩን የምናምን መሆኑን እናረጋግጣለን፡፡ በዚህም መሠረት ታሪካዊው ክርስትና የቤተክርስቲያንን አስፈላጊነት ያምናል፡፡

በዚህ ትምህርት፣ በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ የእምነት አንቀፆች ውስጥ ማዕከላዊ ስፍራ ባላቸው ሁለት ነገረ ጉዳዮች ላይ ብቻ እናተኩራለን፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ፣ በቤተ ክርስቲያን ስለሚኖረን ተሳትፎ እንመለከታለን፡፡ በቤተክርስቲያን ተጠብቀው መቆየት ስለሚገባቸውም አስተምህሮዎች እንመለከታለን፡፡ በቤተክርስቲያን ስለሚኖረን ተሳትፎ በመመልከት እንጀምር፡፡

## ተሳትፎ

የሃይማኖት መግለጫው “በቅድስት … ቤተክርስቲያን አምናለሁ” ሲል፣ በቤተክርስቲያን የመሳተፍን አስፈላጊነት አፅንኦት መስጠቱ ነው፡፡ እርግጥ ነው የክርስቲያናዊ ቤተክርስቲያንን ታሪክ ስንመለከት፣ በርካታ ሰዎች እግዚአብሔር አብ አባታቸው፣ ኢየሱስ ጌታቸው፣ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ጠበቃቸው እንዲሆን ይፈልጋሉ፣ ታዲያ ማን ነው በአንድነት የእግዚአብሔር ሕዝብ ስብስብ የሆነችው የምትታየዋ ቤተክርስቲያን አካል መሆን የማይፈልግ ማን ነው? በዕብራውያን 10፥25 እንደምናነብበው፡

> *በአንዳንዶች ዘንድ ልማድ እንደሆነው መሰብሰባችንን አንተው (ዕብራውያን 10፥25)፡፡*

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

በመጀመሪያው ምዕተ ዓመት እንኳን አንዳንድ አማኞች የምትሰበሰበውን ቤተክርስቲያን የአምልኮ፣ የትምህርትና የኅብረት ማዕከል ከማድረግ ሊያገልሏት ይፈልጉ ነበር፡፡ ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚነግሩን ግን ቤተ ክርስቲያን ለክርስቲያኖች እጅግ አስፈላጊ ናት፡፡

እርግጥ ነው፣ የሐዋርያትን የሃይማኖት መግለጫ በመጀመሪያ ይጠቀሙ የነበሩት ግን እንደዚህ አልነበሩም፡፡ በተቃራኒው፣ የሃይማኖት መግለጫው በውል አገልግሎት ላይ የሚውለው በቤተክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ ነበር፡፡ ለመጠመቅ ወደ ቤተክርስቲያን በሚመጡትም ይረጋገጥ ነበር፡፡ ከጥምቀታቸውም በኋላ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይጨመሩ ነበር፣ በስብሰባዎቿም ይሰተፉ ነበር፡፡ እኛም የሃይማኖት መግለጫውን ከመጠቀም አንፃር እንድንከተለው የተተወልን ተምሳሊት ይኸው ነው፡፡

ዛሬ እኛ በምንኖርበትም ዘመነኛ ዓለም ራሳቸውን ከቤተክርስቲያን የሚያገልሉ ክርስቲያኖች ይገጥሙናል፡፡ ምናልባትም የተደራጀን ሃይማኖት ባለመውደዳቸው ሊሆን ይችላል፡፡ ወይንም በሌሎች ክርስቲያኖች በደል ደርሶባቸው ሊሆን ይችላል፡፡ ወይም ደግሞ ክርስቲያናዊ መጻሕፍትን ማንበብ፣ የክርስቲያን ቴሌቪዥኖችን መከታተልና ክርስቲያናዊ ድረ-ገጾችን መጠቀም ይበቃል ብለውም ሊያስቡ ይችሉ ይሆናል፡፡

ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቲያኖች በገሃድ የምትታይ፣ እውን የሆነች ማኅበረሰብ መመሥረት እንዳለባቸውና ይህችም ማኅበረሰብ ለእያንዳንዱ ክርስቲያን እጅግ አስፈላጊ መሆኗን ያስተምራል፡፡ ምንም እንኳን ክርስቲያኖች በክርስቶስ መንፈሳዊውን ኅብረት እርስ በርስ የሚካፈሉ ቢሆንም፣ ኅብረታቸው ግን ለመንፈሳዊው ነገር ብቻ መሆን አይኖርበትም፡፡ ክርስቲያናዊው ማኅበረሰብ ልክ እንደ አንድ ቤተሰብና እንደ ጎረቤታሞች አብሮ መኖር ይኖርበታል፡፡ ፊት ለፊት በመተያት አብረው የሚኖሩ ሰዎችን ሊያካትት ይገባል፡፡

በቤተክርስቲያን ውስጥ የመሳተፍን አስፈላጊነት በአዕምሯችን ይዘን፣ በቤተክርስቲያን ሊጠበቁ ስለሚገባቸው አስተምህሮዎች እንሻገራለን፡፡

## ጥበቃ

የተማረው ሕዝብ ቁጥር እጅግ አናሳ በሆነበት በመጀመሪያው ምዕተ ዓመት የክርስትና ሕይወት ጉዞ ወቅት፣ የሃይማኖት መግለጫዎችን መልሶ መላልሶ ማሰላሰል፣ መከለስና የእምነትን አቋም በቤተክርስቲያን የመግለጡ ልምምድ እጅግ በጣም ወሳኝ ሚና ተጫውቷል፡፡ በዚህም ዘመን ካመኑት መካከል ማንበብ የሚችሉት በጣም ጥቂቶቹ ብቻ ሲሆኑ፣ ከሚያነቡትም መሃል የራሳቸው መጽሐፍ ቅዱስ የነበራቸው በጣም ጥቂቶች ነበሩ፡፡ ስለዚህም የሃይማኖት መግለጫዎችን በአምልኮ ፕሮግራሞች ላይ በአደባባይ በአንድነት የማሰማቱ ልምምድ እጅግ ወሳኝ ሚና የነበረው ሲሆን ቅዱሳት መጻሕፍት እንዴትና በምን

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

> መልክ በአንድነት እንደተሰባሰቡ ትክክለኛውን መረዳት ለማስጨበጥና የእምነት አንቀጽ ብለን የምንጠራውን ወይም የተደነገገ የእምነት መግለጫን መጠነ ልክ ለማመልከት ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡ [ዶ/ር ጆናታን ፔኒንግተን]

ስለ እምነት አንቀጽ ስንነጋገር እንደጠቀስነው፣ ቤተክርስቲያን የማትሻር አይደለችም፡፡ የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫም አጥቢያ ቤተክርስቲያናችን የምታስተምረንን ሁሉ እንድናምን አያበረታታንም፡፡ በምትኩ ግን፣ ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን ሃላፊነት የሰጣት በተወሰነ መልክ አስተምህሮዎችን እንድትጠብቅና ወንጌልንና ሌሎችን እውነቶች እንድታውጅ ነው፡፡

የኢየሱስ ወንድም የነበረው ይሁዳ፣ ስለ ቤተክርስቲያን ተልዕኮ በቁጥር 3 እና 4 እንዴት እንደገለጠ እንመልከት፡፡

> ወዳጆች ሆይ፥ ስለምንካፈለው ስለ መዳናችን ልጽፍላችሁ እጅግ ተግቼ
> ሳለሁ፥ ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ስለ ተሰጠ ሃይማኖት እንድትጋደሉ
> እየመከርኋችሁ እጽፍላችሁ ዘንድ ግድ ሆነብኝ።
> ከብዙ ጊዜ በፊት ለዚህ ፍርድ የተጻፉ አንዳንዶች ሰዎች ሾልከው
> ገብተዋልና፤ ኃጢአተኞች ሆነው የአምላካችንን ጸጋ በሴሰኝነት ይለውጣሉ
> ንጉሣችንንና ጌታችንንም ብቻውን ያለውን ኢየሱስ ክርስቶስን ይክዳሉ።
> (ይሁዳ 3-4)

እንደ ይሁዳ አገላለጥ፣ ከቤተክርስቲያን ሥራዎች መካከል ለእምነት መጋደል፣ እውነትን ከስህተት አስተምህሮዎችና ልምምዶች መከላከል እንደሚገኙበት እንረዳለን፡፡

ዛሬም በእኛ ዘመን፣ በተለያዩ የቤተክርስቲያን አካላት ውስጥ የተለያዩ የስህተት አስተምህሮዎች መኖራቸው ለአብዛኛዎቻችን ግልጥ ነው፡፡ በተጨማሪም በርካታ የኃጢአት ልምምዶችም አሉ፡፡ ሆኖም ግን፣ እግዚአብሔር የቤተክርስቲያንን ሃላፊነት ጨርሶ አልነጠቀም፣ ወይንም እውነተኛውን አስተምህሮ የመጠበቅን ሥራ ሌላ ቡድን ወይም ግለሰብ እንዲረከብ አላወጀም፡፡ ዛሬም ቢሆን እውነትን የመጠበቁ ሃላፊነት የቤተክርስቲያን ሥራ ነው፡፡

ቤተክርስቲያን አሁንም ይህንኑ ሥራ ለመሥራት እየሞከረች ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ከሌሎቹ በተሻለ መንገድ እናከናውነዋለን፡፡ ጥቂቶቹ ነገረ-መለኮቶቻችን ለቅዱሳት መጻሕፍት ታማኝ ናቸው፣ አንዳንድ ክፍሎቹ ግን መሻሻል ይኖርባቸዋል ወይንም ሁሉም በጠቅላላ ይለወጣሉ፡፡ እንግዲህ ዘወትር ጉዳዩ ይህ ሊሆን ይገባዋል፡፡ በዚህ ትምህርት ያነገብነው ዓላማና ግልጽ ማድረግ የምንሻው ነጥብ ግን ጨርሶ እጅ የማንሰጥ መሆኑን ነው፡፡ በቤተክርስቲያን ውስጥ አስተምህሮዎችን በጽናት እንጠብቃለን፡፡ ይህንን ቸል ካልን ግን በቤተክርስቲያን አምናለሁ የሚለውን የታሪካዊ ክርስትና ማዕከላዊ የእምነት አንቀጽ ቸል ማለታችን (ማቃለላችን) ነው፡፡

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

ስለ እግዚአብሔርና ስለ ቤተክርስቲያን የተጠቀሱትን የእምነት አንቀጾች ከተመለከትን፣ አሁን ደግሞ ወደ ሦስተኛው ጎራ ማለትም በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ውስጥ ስለ ድነት የተጠቀሱትን ወደ መመልከቱ ለመሻገር እንዘጋጃለን፡፡

# ድነት

> *የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ስለ ድነት ብዙ የሚናገረው በስተመጨረሻው ላይ ነው፡፡ አንዳንድ ሰዎችም ሌላ ቦታ ከማድረግ ይልቅ መጨረሻ በማስቀመጡ ግር ይላቸዋል፡፡ በመሠረቱም ለምን እንደዚያ እንደሆነ የሃይማኖት መግለጫው ራሱ ምክንያቱን አይነግረንም፡፡ በአንክሮ ከተመለከትነው ግን፣ ለእኔ የሚመስለኝ፣ የሃይማኖት መግለጫው ትምህርተ እግዚአብሔርን፡ አብን፣ ወልድን እና መንፈስ ቅዱስን በጽኑ መደላደል ላይ ማኖርን ዓላማው ማድረግ የፈለገ ይመስላል፡፡ ይህንንም ማሳየት የወደደው ድነት የሚመነጨው ከሌላ ከየትኛውም ሰብዓዊ ጥበብ ወይንም ምንጭ ሳይሆን ከእግዚአብሔር ብቻ መሆኑን በእርግጠኝነት ለማመልከት ነው፡፡ እግዚአብሔር አብ፣ እግዚአብሔር ወልድ እና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ማን እንደሆኑ ማወቅ ኃጢአታችንን ብንናዘዝ እንደምንድን ወደ ተሰጠው ተስፋና ጥሪ እንድንቀርብ ያስችለናል፡፡ እኔ እንደማስበው እነዚህ አረፍተ ነገሮች በስተመጨረሻው ላይ መቀመጣቸው ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት ፍሬው የሚወጣው በስላሴ ውስጥ ከሚገኘው ከእግዚአብሔር ማንነት ውስጥ ነው፡፡ [ዶ/ር ስቲቭ ሃርፐር]*

በሃይማኖት መግለጫው ውስጥ የሚገኙት ሦስቱ የእምነት አንቀጾች ስለ ድነት የሚናገሩ ናቸው፡፡ በተለይም፣ የኃጢአትን ስርየት፣ የሥጋን ትንሣኤ፣ የዘላለምን ሕይወት ያነሳሉ፡፡ በትፊታዊው ሲስተማቲክ ቲዮሎጂ፣ ትንሣኤና የዘላለም ሕይወት የተቀመጡት በነገረ ፍጻሜ፣ ርዕስ ስር ነው፡፡ እኛ ግን ነገሩን በቀላሉ ለማቅረብ ያመች ዘንድ በድነት ርዕስ ስር ለመዳሰስ እንሞክራለን፡፡

ሁሉም ክርስቲያኖች የኃጢአት ይቅርታ የሚገኘው በክርስቶስ ደም የማንጻት ጉልበት መሆኑን ያምናሉ፡፡ በኃጢአታችን ከተናዘዝንና ንስሓ ከገባን፣ በእነርሱ ምክንያት እግዚአብሔር ወደ ሲኦል አይከተንም፡፡ የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ እንደሚያመለክተውም፣ ይህ እምነት ከቤተክርስቲያን ቀደምት ዓመታት አሰንስቶ የምታስተምረው ትምህርት እንደነበር እንረዳለን፡፡ ከቅዱሳት መጻሕፍት እንደምንማረውም ይቅርታን ያገኙ ሁሉ በክርስቶስ ኢየሱስ በዘላለም ሕይወት በረከት የተባረኩ መሆኑን ሁላችንም እናውቃለን፡፡ ለአብነት ያህል፣ ዮሐን 3፥16-18 እነዚህን በመሰሉ ቃላት ያበረታታናል፡

> በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ፥ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም አልላከውምና።
በእርሱ በሚያምን አይፈረድበትም፤ በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ስላላመነ አሁን ተፈርዶበታል።

የዘላለም ሕይወት ላመነ ሁሉ ተሰጥቷል፡፡ የሚጀምረውም ወደ እምነት ከመጣንበት ጊዜ ጀምሮ ነው፡፡ ነፍሳችን አዲስ ሕይወት እስካገኘች ድረስ አትሞትም፡፡

ነገር ግን በሃይማኖት መግለጫው የተጠቀሰው የዘላለም ሕይወት ባሕርይ (ተፈጥሮ) ዘመነኞቹን ክርስቲያኖች አልፎ አልፎ ያስገርማቸዋል፡፡ በተለይም፣ የሃይማኖት መግለጫው ስለ ሥጋ ትንሣኤ ይናገራል፡፡ ክርስቲያኖች ግን አንዳንድ ጊዜ ይህ ስለ ክርስቶስ ትንሣኤ ነው የሚናገረው በማለት ስህተት ይፈጽማሉ፡፡ ይህ ግን በሃይማኖት መግለጫው ውስጥ "በሦስተኛውም ቀን ከሙታን እንደተነሣ" ተብሎ ቀደም ብሎ የተጠቀሰው አይደለም፡፡ ይህ የእምነት አንቀጽ ጨርሶ አልተደገመም፡፡ ይልቁኑ፣ የሃይማኖት መግለጫው ስለ ሙታን ትንሣኤ ሲናገር፣ በፍርድ ቀን፣ የሰው ዘር ሁሉ እንደሚነሣ፣ ከዚያም ወደ ዘላለም ዕጣ ፈንታቸው እንደሚሄዱ፣ ይህም አካል ባልለበሰ መንፈስ ሳይሆን፣ አካላዊ ስብእና ባለው ማንነት እንደሚነሱ የሚያስተምረውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ የሚያመለክት ነው፡፡ ይህም የቅዱሳት መጻሕፍት የማያወላውል አስተምህሮ ሲሆን፣በሺዎች ለሚቆጠሩ ዓመታትም የቤተክርስቲያን የእምነት አንቀጽ ሆኖ ዘልቋል፡፡

ኢየሱስ በዮሐንስ 5፥28-29 እንዳስተማረው:

በመቃብር ያሉቱ ሁሉ ድምፁን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል፤ መልካምም ያደረጉ ለሕይወት ትንሣኤ ክፉም ያደረጉ ለፍርድ ትንሣኤ ይወጣሉና በዚህ አታድንቁ።

ስለ ድነት በሃይማኖት መግለጫው የተቀመጡት አንቀጾች በቅዱሳት መጻሕፍትም በግልጽ የተቀመጡ አስተምህሮዎች ናቸው፡፡ ምንም እንኳን፣ ክርስቶስን እንከተላለን የሚሉ የዘመናችን ክርስቲያኖች እነዚህን መሠረታዊና ወሳኝ አስተምህሮዎች ባይቀበሉዋቸውም በመጽሐፍ ቅዱስ አማኝ ቤተክርስቲያናት ተከብረው ተጠብቀዋል፡፡ ጥቂቶች ደግሞ እግዚአብሔር ስለ ኃጢአታችን አይጠይቀንም፣ ስለዚህም ይቅር መባል አያስፈልግም ይላሉ፡፡ በላይ ይኖራል የሚባለው ሕይወት በዚህ የምንኖረው ነው፣ "የዘላለም ሕይወት" እንወርሳለን የሚባለውም በዚህ በምድር ዘመናችን በምንኖረው ሕይወት የተወሰነ ነው የሚሉ የማያምኑ ሰዎች በእኛ ቤተክርስቲያን ውስጥ አሉ፡፡ በርካቶቹ ደግሞ በመንግሥተ ሰማያት የምንኖረው አካል የለሽ መናፍስት ብቻ ሆነን ነው በማለት የተሳሳተ እምነት ይዘዋል፡፡ እንግዲህ፣ የሃይማኖት

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

መግለጫው በቀደመው ዘመን ለነበረችው ቤተክርስቲያን ወሳኝ እንደነበረው ሁሉ ለዛሬዪቱም ቤተክርስቲያን አግባብነት ያለውና አስፈላጊ ነው የምንለው እነዚህን በመሳሰሉ ምክንያቶች ነው፡፡

በማጠቃለያው፣ የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫው ከእግዚአብሔር፣ ከቤተክርስቲያንና ከድነት ጋር በተያያዙ አስተምህሮዎች ላይ ያተኩራል፡፡ በዚህ የተከታታይ ትምህርት መድብላችን ውስጥ ወደፊት በምንመለከታቸው ትምህርቶች፣ እያንዳንዳቸውን ሃሳቦች በጥልቀት እንመለስባቸዋለን፡፡ ለአሁኑ ግን፣ እነዚህ መሠረታዊ አስተምህሮዎች የክርስትናን ወሰነ ድንበር ለበርካታ መቶና ሺህ ዓመታት ውጤታማ በሆነ መንገድ ጠብቀውና ግልጽ አድርገው የኖሩ የመሆኑን ትልቅ ምስል በቀላሉ ለማሳየት እንሻለን፡፡

የሐዋርያትን የሃይማኖት መግለጫ እንደ እምነት አንቀጻችን በተመለከትንበት ትምህርታችን ውስጥ፣ ስለ ሃይማኖት መግለጫው ታሪክ የተነጋገርን ሲሆን ነገረ-መለኮቱንም በወፍ በረር ለመዳሰስ ሞክረናል፡፡ አሁን ደግሞ ወደ አራተኛውና በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ የተጠቀሰውን የእምነት አንቀጽ ያልተቋረጠ ጠቀሜታ ወደምንመለከትበት ዓቢይ ርዕስ እንሻገራለን፡፡

# 4. ጠቀሜታ/ አስፈላጊነት

በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ውስጥ ስለተጠቀሱት አስተምሮአዊ አንቀጾች ጠቀሜታ ሦስት ዘርፎችን እንዳስሳለን፡፡ በመጀመሪያ፣ እነዚህ አስተምህሮዎች ለተቀሩት የክርስቲያናዊ ነገረ-መለኮት ዘርፎች መሠረታዊ መሆናቸውን እንመለከታለን፡፡ ሁለተኛ፣ በቤተክርስቲያን የታሪክ ዘመናት ሁሉ እነዚህ አስተምህሮዎች ያገኙትን ዓለም አቀፋዊ ይሁንታ እንመለከታለን፡፡ ሦስተኛ ደግሞ፣ እነዚህ የእምነት አንቀጾች ያላቸውን የአንድነት ተፈጥሮ እንነጋገርበታለን፡፡ እስኪ በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ውስጥ እነዚህ አስተምህሮዎች ያላቸውን መሠረታዊ ብቃት በመዳሰስ እንጀምር፡፡

## መሠረታዊነት

አብዛኛዎቹ ሰዎች ትላልቅ ሕንፃዎች ጠንካራ መሠረት ያስፈልጋቸዋል ከሚለው ሃሳብ ጋር ይተዋወቃሉ፡፡ መሠረት የተቀረው የሕንፃው አካል የሚገነባበት መነሻ ነው፡፡ የህንጻውን አካላት በየስፍራቸው አጥብቆ የሚይዝ እና ለአጠቃላዩ ውቅር ብርታትና ጥንካሬን የሚያጎናጽፍ መልሕቅ ነው፡፡ በኤፌ 2፥19-21 ጳውሎስ በነቢያትና በሐዋርያት መሠረት ላይ ስለተመሠረተችው ቤተክርስቲያን ይናገራል፡፡

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

እንግዲያስ ከእንግዲህ ወዲህ ከቅዱሳን ጋር ባላገሮችና የእግዚአብሔር ቤተ ሰዎች ናችሁ እንጂ እንግዶችና መጻተኞች አይደላችሁም።
በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል፥ የማዕዘኑም ራስ ድንጋይ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤
በእርሱም ሕንጻ ሁሉ እየተጋጠመ በጌታ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንዲሆን ያድጋል፤

ያለ እውነተኛና ጠንካራ መሠረት፣ ቤተክርስቲያን እግዚአብሔርን በሚያከብር መንገድ ልትገነባ አትችልም፡፡

በተመሳሳይም መንገድ፣ ክርስቲያን ነገረ-መለኮት እግዚአብሔርን በሚያከብርና ለሕዝቡም በሚጠቅም መንገድ በእውነተኛ አስተምህሮዎች ላይ ሊመሠረት ይገባል፡፡ ኢየሱስ የቤተክርስቲያን የማዕዘን ድንጋይ እንደሆነ ሁሉ፣ ትምህርቶቹም የነገረ-መለኮት የማዕዘን ድንጋይ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ሐዋርያትና ነቢያት ክርስቶስን ለዓለም በመስበክ የቤተክርስቲያን መሠረት እንደሆኑ ሁሉ፣ የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫም በቅዱሳት መጻሕፍት የተመዘገቡትን የሐዋርያት ትምህርቶች ስለሚያስተዋውቅ የነገረ-መለኮት መሠረት ነው፡፡

*የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ውበቱ በዚህ ዘመን የምንገኝ በርካታ የተለያዩ ቤተ እምነቶች ያለን ክርስቲያኖች ይሁንታ ልንሰጣቸው የሚገቡ ወሳኝ ክርስቲያናዊ አስተምህሮዎችን የእግዚአብሔር ማንነት፣ የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት፣ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ይህም በትምህርተ ድነት ውስጥ እንዴት እንደሚሠራ፣ ቤተክርስቲያን፣ የመጨረሻው ፍርድ እና የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት በተሳካ መንገድ ጠቅለል አድርጎ መያዙ ነው፡፡ እነዚህ ክርስቲያናዊ አስተምህሮዎች ከሌሉዋችሁ በስተቀር እውነተኛ ክርስቲያናዊ እምነት ሊኖራችሁ አይችልም፡፡ [ዶ/ር ስቴፈን ዌሉም]*

የሐዋርያትን የሃይማኖት መግለጫ የመሠረታዊነት ተፈጥሮ በሁለት ክፍሎች እንገነዘባለን፡፡ በመጀመሪያ፣ ሌሎቹ አስተምህሮዎች ሊበየኑ የሚችሉባቸውን ደረጃዎች እንዴት እንደሚያወጣ እንመለከታለን፡፡ ሁለተኛ፣ ሌሎች እውነተኛ አስተምህሮዎች የሚመሠረቱበት አመክንዮአዊ መሠረት ሆኖ እንዴት እንደሚያገለግል እንነጋገራለን፡፡ እስኪ የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫው የነገረ-መለኮት ሚዛንነቱን (ልኬትነቱን) እንመልከት፡፡

## ሚዛንነት / ደረጃ

የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ እንደ አስተምህሮአዊ ሚዛን ያገለግላል ምክንያቱም የክርስትናን ወሳኝና ታላላቅ ሃሳቦችን ይዟልና፡፡ እነዚህም ሃሳቦች በቅዱሳት መጻሕፍት በግልጽ የተቀመጡ ትምህርቶች ሲሆኑ እያንዳንዱ ሰው የራሱ ሊያደርጋቸውና ሊቀበላቸው የሚገቡ ናቸው፡፡ በዚህ

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

ትምህርት ቀደም ብለን እንደተመለከትነው፣ እነዚህ ትምህርቶች ለክርስትና ወሳኝ ናቸው፡፡ ስለሆነም፣ የራሳችን ልናደርጋቸው የተገቡ ሌሎች አስተምህሮዎች ሁሉ ከእነዚህ ትምህርቶች ጋር የሚጣጣሙ ሊሆኑ ይገባቸዋል፡፡ ከእነዚህ ትምህርቶች ጋር የሚጣረስ ምንም ዓይነት ሃሳብ ጨርሶ አንቀበልም፡፡

በሰው እጅ እንቅስቃሴያቸው ቁጥጥር የሚደረግበትና የአንድን እንስሳ ምስል ለብሰው የሚናገሮ አሻንጉሊቶችን ታውቃላችሁ? እነዚህ አሻንጉሊቶች በተዋጣለት እንቅስቃሴ ከሌላ ወገን ተቀርፆ ከተቀነባበረ ድምጽ ጋር ተዋህደው የሚናገሩ እንዲመስሉ ይደረጋሉ፡፡ ምንም ያህል የተቀነባበረና የተዋጣለት እንቅስቃሴ ቢያደርጉም ንግግሩን የሚያደርጉት እነዚያ እንስሶች እንዳልሆኑ እናውቃለን ምክንያቱም አሻንጉሊቶች ሕያው አይደሉምና፡፡ ስለዚህ አሻንጉሊቶች ሲናገሩ ስንሰማና ስንመለከት በእርግጥ የሚናገሩት አሻንጉሊቶቹ እንዳልሆኑ እናውቃለን ይህንንም የምንረዳው ከዚህ ቀደም በውል የምናውቀው እውነታ ስላለና ያ እውነት ሚዛን ሆኖ ስለሚያገለግለን ነው፡፡

በተመሳሳይም መንገድ የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ በፍጹም ልንቀይራቸው የማንችላቸውን አጽንተን የምንይዛቸውን ማዕከላዊ የእምነት አቋሞች ጠቅለል አድርጎ ያቀርብልናል፡፡ ከእነዚህም ነጥቦች አንፃር መጽሐፍ ቅዱሳችን በጣም ግልጽ አድርጎ የሚያስቀምጥልን እጅግ አስፈላጊ መሆናቸውን ነው፣ ስለዚህም እነርሱን በተመለከተ በምንም መንገድ አናመቻምችም፡፡ ስለዚህም ምንም ሰው ምንም ዓይነት አስተሳሰብ ቢያቀርብልን፣ ከእነዚህ የቅዱሳት መጻሕፍት ማዕከላዊ አስተምህሮዎች ጋር የሚጣረስን የትኛውንም ሃሳብ አናምንም፡፡

የሃይማኖት መግለጫችንን እንደ ሚዛን መጠቀማችን የስህተት አስተማሪዎች አሳማኝ የሚመስል ክፉ ነገረ-መለኮት ይዘውልን ሲቀርቡ ለቅዱሳት መጻሕፍት ታማኝ ሆነን እንድንዘልቅ ይረዳናል፡፡ የተዋጣላቸው የመከራከሪያ ነጥቦች ያሉዋቸው፣ እንደ ግለሰብም ማራኪ የሆኑና እየተሳሳቱና እየዋሹ እንኳን የሚናገሩዋቸውን አብዛኛዎቹን ነገሮች ወደማመን እንድናዘነብል የሚስቡን ሰዎች ይገጥሙናል፡፡ ስለዚህ፣ በቅዱሳት መጻሕፍት አስተምህሮ ላይ መሠረታችንን የሚያጠብቅልን መሠረታዊ የእምነት አንቀጾችን አጠርና ጠቅለል አድርጎ የሚያቀርብልን መልህቅ ያስፈልገናል፡፡ የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫም ይህንን መልህቅ ያቀርብልናል፡፡

ለምሳሌ ያህል፣ ቤተክርስቲያን ገና በመጀመሪያዎቹ ዓመታቶቿ ምላሽ የሰጠችባቸው በርካታ ዋና ዋና የስህተት አስተምህሮዎች ነበሩ፡፡ ከእነዚህም አንዱ ኖስቲሲዝም ነበር፡፡ ከሌሎቹ ነገሮች በተጨማሪ፣ ኖስቲሲዝም አካላዊ ሰውነታችን ርኩስ ነው፣ ድነት ነፍሳችንን በሰውነታችን ከተያዘችበት ከእዚህ እስረኝነት ነፃ ያወጣታል የሚል ነው፡፡ እንግዲህ በመጀመሪያዎች ዓመታት የነበሩት ክርስቲያኖች ሁሉ ይህንን ስህተት ለመቃወም የሚችሉበት እውቀት ሊኖራቸው አይችልም፡፡ ሆኖም ግን በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ የሰለጠኑ ሰዎች ግን ቅዱሳት መጻሕፍት የሚያስተምሩትን የሥጋ ትንሣኤ መሠረት በማድረግ ይህንን የሰላ ስህተት በፍጹም

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

እርግጠኝነት ውድቅ ያደርጉታል፡፡ ይህም፣ ኢየሱስ ሁለንተናችንን ሊቤዥ መጥቷል፣ ይህም ነፍሳችንን ብቻ ሳይሆን፣ አካላችንንም ያካትታል ብሎ የሚያስተምረውን ማለት ነው፡፡

አብዛኛዎቻችን ስልጡን በሆኑ ክርክሮች በቀላሉ ግራ እንጋባለን ወይንም በተሳሳተ አሊያም ያለአግባቡ በቀረበ ማስረጃ ከመስመር እንወጣለን፡፡ መቼም ዘወትር በእነዚህ ክርክሮችና ግኝት ተብዬዎች ላይ ማብራሪያ መስጠት አንችልም፡፡ ይሁንና ግን ከሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ጋር የሚጣረሱ ነገሮችን ግን ያለ ማመቻመች በልበሙሉነት ውድቅ እናደርጋቸዋለን፣ ምክንያቱም የሃይማኖት መግለጫ ለቅዱሳት መጻሕፍት ታማኝ ነውና፡፡

እርግጥ ነው የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫንም ሆነ የትኛውንም የእምነት አንቀጽ ወደ ቅዱሳት መጻሕፍት ደረጃ ልናደርሰው ፈጽሞ አንሻም፡፡ ፈጽሞ ሊጠየቅ የማይችለው መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው፡፡ በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ውስጥ የተቀመጡት የሃይማኖት መግለጫዎች እንኳን ሳይቀሩ ከቅዱሳት መጻሕፍት ጋር የሚጣረሱ መሆናቸው ከታየ ውድቅ ሊደረጉ ይችላሉ፡፡ የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ግን ገና ከመጀመሪያው የቤተክርስቲያን ዘመን አንስቶ እስከ አሁን ድረስ በጊዜ ተፈትኖ አልፏል፡፡ ስለዚህ፣ በእኛ ዘመን የሚያጋጥሙንን በርካታ አስተምህሮዎች መርምረን ብይን ለመስጠት እንደሚዛን ሊያገለግለን ይችላል፡፡

የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ጠቃሚ የአስተምህሮ ሚዛን ሆኖ እንደሚያገለግለን ከተመለከትን፣ አሁን ደግሞ ሌላኛውን መሠረታዊ የሆነውን ክፍሉን ለመመልከት እንዘጋጃለን፡፡ ይህም የሌሎቹ ነገረመለኮታዊ አተያዮች አመክንዮአዊ መሠረት ሆኖ የሚገለግል መሆኑን የምንመለከትበት ነው፡፡

## አመክንዮአዊ መሠረት

በሃሳቦች መካከል ያለው አመክንዮአዊ ግንኙነት ከወንዝና ከምንጩ ወይንም ከዋናው መገኛው ውሃ ጋር ካለው ግንኙነት ጋር ይመሳሰላል፡፡ አመክንዮአዊ መሠረታዊ ሃሳቦችም ልክ እንደውሃው ዐቢይ ምንጭ ናቸው፡፡ የሌሎች ሃሳቦች ምንጮች ናቸው፡፡ አመክንዮአዊ ጥገኛ ሃሳቦች ደግሞ ልክ ከዋናው ምንጭ ተፈጥሮአዊ በሆነ መንገድ እንደሚፈስሰው ወንዝ ናቸው፡፡ እንግዲያው፣ አንዱ ሃሳብ ለሌላኛው አመክንዮአዊ መሠረት ሆኖ ያገለግላል ብለን ስንል፣ አመክንዮአዊ መሠረታዊ ከሆነው ሃሳብ ውስጥ የሚወጣ አመክንዮአዊ ጥገኛ የሆነ ሃሳብ ልንገነባበት የምንችለው ምክንያታዊ መከራከሪያ ሃሳብ መፍጠር እንችላለን ማለታችን ነው፡፡ ለምሳሌ፣ የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫው ስለ እግዚአብሔር አብ ለይቶ የሚናገረው ነገር በጣም ጥቂት ነገር ብቻ ነው፡፡ የሚናገረውም በጠቅላላው፡-

> እኔ ሁሉን በሚችል፣ ሰማይንና ምድርን በፈጠረ
> በእግዚአብሔር አብ አምናለሁ፡፡

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

የሚል ብቻ ነው፡፡

ሆኖም ግን እነዚህ አስተምህሮዎች ስለ አብ ለምንማራቸው ሌሎች በርካታ ነገሮች አመክንዮአዊ መሠረት ይጥሉልናል ማለት ነው፡፡ ለአብነት ብንጠቅስ፣ እግዚአብሔር የሰማይና የምድር ፈጣሪ ነው በሚለው መሠረት ላይ ቆመን፣ በሰማይና በምድር ሥልጣን ያለው መሆኑን፣ የመጀመሪያው ተፈጥሮ መልካም የነበረ መሆኑን፣ ፍጥረታዊውን ዓለም በመመልከት ስለ እግዚአብሔር ብዙ ነገሮችን መማር እንደምንችል የማመን መብት ይኖረናል፡፡

አመክንዮአዊ መሠረታዊ የሆኑ ሃሳቦችን በዛፍ መስለን መግለጥ እንችላለን፡፡ መሬቱን እንደ ቅዱሳት መጻሕፍት ብንወስደው ዛፉን ደግሞ ከውስጣቸው እንደሚበቅለው ነገረ-መለኮት ልንቆጥረው እንችላለን፡፡ የዛፉ ግንድና ዋና ዋና ቅርንጫፎቹም፣ እጅግ መሠረታዊ የሆኑ አስተምህሮዎችን ይወክላሉ፡፡ እነዚህም በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ ብቻ የሚደገፉ ይሆናሉ፡፡ ሆኖም ዋናዎቹ ቅርንጫፎች ወደ በርካታ ትናንሽ ቅርንጫፎች ሲበታተኑ ግን፣ ከዋናው ቅርንጫፍ አመክንዮአዊ መሠረት ባለው መንገድ ወደሚያድጉ የእምነት አቋሞች ይበራከታሉ፡፡ ቅጠሎቹን ደግሞ ስንመለከት፣ ለትናንሾቹ ቅርንጫፎች ጥገኛ የሆኑ ሃሳቦችን እንድንመለከት ያደርጉናል፡፡ በዚህ መንገድ ስዕሉን ስናስቀምጠው፣ ከሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ የመጀመራችንን ዋጋ በግልጽ እንመለከተዋለን፡፡ በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ በጥልቀት የተመሠረተውን፣ የዛፉን ትክክለኛ ቅርጽ ለማግኘት አስቀድመን ዋናዎቹን አስተምህሮዎች መማር ይገባናል፡፡

ይህ ነገር ለእኛ ሁለት ነገሮችን ያከናውንልናል፡፡ በመጀመሪያ፣ በነገረ-መለኮታዊ ስርዓቶቻችን ውስጥ ባሉት ልዩ ልዩ የእምነት አቋሞች መካከል ያለውን ግንኙነት እንድንመለከት ይረዱናል፡፡ ሁለተኛ፣ ጥቃቅኖቹ ሃሳቦች ከቅዱሳት መጻሕፍት ጋር ስር የሰደደና ዘመናትን የዘለቀ ትስስር ካላቸው ከዋናዎቹ የእምነት አቋሞቻችን ሊጣጣሙ በሚችሉበት መንገድ እንድናስብ ይረዱናል፡፡

> *በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ውስጥ የሚገኙ አስተምህሮዎች የክርስቲያናዊ እውነትን ፍሬ ነገር ጽኑ መሠረት እንዲኖረው ያደርጉታል፡፡ የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ከሁለተኛው ምዕተ-ዓመት አንስቶ የሚቆጠር ዕድሜ ያለው ሲሆን፣ በሁለተኛውም ምዕተ-ዓመት የተለያዩ ቅርጾች ነበሩት በመጨረሻም እኛ ዛሬ የምንገለገልበትን ዓይነት ቅርጽ ይዟል፡፡ በዚያም ውስጥ ስላሴን ታገኛላችሁ፣ አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ፡፡ የጌታ ኢየሱስን ትስጉት፣ ቤዛዊ ሞትና ድል ነሺ ትንሣኤ እና ዳግም ምፅዓት ታገኛላችሁ፡፡ የኃጢአትንም ስርየት ታገኛላችሁ፡፡ በክርስቶስ ዳግም የተወለዱ ቅዱሳን ኅብረት የሆነችውን ቤተክርስቲያንን ታገኛላችሁ፡፡ በእኔ አመለካከት እነዚህን አስተምህሮዎች አጉልቶ የሚያወጣ ጤናማ የሆነና የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ያህል ዕድሜ ጠገብ ሥራ ያከናወነ መግለጫ በየትኛዋም ቤተክርስቲያን ይገኛል ብዬ አላስብም፡፡ [ዶ/ር ጄ.አይ.ፓከር]*

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫን ጠቀሜታ ከመሠረታዊነት ተፈጥሮው አንፃር ተመልክተነዋል፣ አሁን ደግሞ የእርሱን አስተምህሮዎች ዓለም አቀፋዊ ይሁንታ ማግኘትን ወደ መመልከቱ እንሻገራለን፡፡

# ዓለም አቀፋዊነት

የጭብጦችን እውነታ ከምንበይንባቸው መንገዶች አንዱ የተለያዩ ምስክሮች የተናገሩትን መመልከት ነው፡፡ ብዙ ምስክሮች እውነትነቱን ያመለከቱለትን ሃሳብ እኛም ወደማመኑ እናዘነብላለን፡፡ ለነገረ-መለኮትም እውነቱ ይኸው ነው፡፡ እንግዲያው እኛም ልናምንበት የሚገባውን ነገር ለመወሰን፣ በየታሪክ ዘመናቱ የኖሩ ሌሎች ሰዎች ያምኑባቸው የነበሩትንና በእኛም ዘመን የሚኖሩ የሚያምኑባቸውን በአፅንኦት መመልከቱ ይረዳል፡፡ ነገሩን ወደ ሐዋርያት የእምነት መግለጫ ስናመጣውም፣ የያዛቸው አስተምህሮአዊ መግለጫዎች በአብዛኛዎቹ የዓለም ክፍሎች በሚገኙ አብላጫ ክርስቲያኖች ዘንድ ይሁንታን ያገኙ ናቸው፡፡

የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫን የእምነት አንቀጾች ዓለም አቀፋዊ ተፈጥሮ በሦስት ታሪካዊ ክፍለ ጊዜያት እንመረምረዋለን፡፡ በመጀመሪያ፣ እነዚህ የእምነት አቋሞች አዲስ ኪዳንን መሠረት ያደረጉ መሆኑን እናያለን፡፡ ሁለተኛ፣ ባለፉት የቤተክርስቲያን የታሪክ ዘመናቶች በነበሩ አብላጫ ክርስቲያኖች ይሁንታን ያገኙ መሆኑን እናያለን፡፡ ሦስተኛ፣ በአሁኑ ዘመን ባለችውም ቤተክርስቲያን ይህንኑ ባህርያቸውን ይዘው እንዴት እንደዘለቁ እናያለን፡፡ በአዲስ ኪዳንና፣ ለእነዚህ አስተምህሮዎች የሚሰጠውን ይሁንታ በመመልከት እንጀምር፡፡

## አዲስ ኪዳን

ከቤተክርስቲያን ቀደምት ዓመታት ጀምሮ፣ በክርስቶስ እና በሐዋርያት ትምህርቶች ላይ አለመስማማቶች ነበሩ፡፡ አንዳንዶቹ አለመስማማቶች ከቤተክርስቲያን ውጪ የሚመጡ ሲሆን አንዳንዶቹ ግን ከውስጥ የሚነሱ ነበሩ፡፡ ለምሳሌ ያህል፣ ገላትያ ምዕራፍ 5 ውስጥ እንደምናነብበው በክርስቶስ አምነው የተለወጡና ከአህዛብ ወገን የሆኑ ክርስቲያኖች እንዲገረዙ ግድ ስለሚሉት ከአይሁድ ወገን የሆኑትን ክርስቲያኖች በመቃወም ይጽፋል፡፡ 2ጴጥሮስ ምዕራፍ 2 ላይ፣ የሃሰት መምህራን በቤተክርስቲያን ውስጥ እንደሚነሱ ጴጥሮስ ያስጠነቅቃል፡፡ አዲስ ኪዳን ኢየሱስ እና ሐዋርያት የተለያዩ ሰዎችን የተሳሳቱ ሃሳቦች ባረሙባቸው ምሳሌዎች የተሞላ ነው፡፡

በቤተክርስቲያን ወሳኝ የሆኑ የእምነት አቋሞች ለድርድር መቅረብ ሲጀምሩ ስህተቶች አደገኛ ይሆናሉ፡፡ ኢየሱስና የአዲስ ኪዳን ጸሐፍት መሠረታዊ በሆኑ ነገረ-መለኮታዊ ነጥቦች ላይ የሚታዩ ስህተቶችን ማረም ግድ ይላቸው የነበረው በዚህ ምክንያት ነው፡፡ እርምቱን በሚያደርጉበት ጊዜ ግን፣ እርስ በርሳቸው ፍፁም ስምም የነበሩ መሆናቸው አጽንዖት የሚሰጠው

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

ጉዳይ ነው፡፡ በርካታ የሃሰት ትምህርቶች በሞሉበት በዚህም ዘመን፣ አዲስ ኪዳን ፈጽሞ የማይሻር አስተምህሮአዊ አንድነትን ለሁሉ በግልጽ ያሳያል፡፡

> *ቤተክርስቲያን እነዚህን መጻሕፍት ያካተተ ቀኖና /canon/ ረጅም ምዕተ ዓመታትን ወስዳ ያወጣችበት እውነታ፣ የአንድ አፍታ ፈጣን ሂደት አልነበረም፡፡ ይህም የሚያመለክተን ቤተክርስቲያን በምትሰጠው ብይን ውስጥ የአንድነት ጽኑ መሠረት ያለ መሆኑን ነው፡፡ ይህም በቀላሉ ወዲያ ልንጥለው የማንችልና፣ እንደ እውነቱ ከሆነም፣ ይህ ብይን ላለፉት 2000 ዓመታት የምሁራን ብይን ሆኖ የዘለቀ ነው፡፡ ሆኖም ግን፣ በአዲስ ኪዳን መዛግብት መካከል የአንድነት ጽኑ መሠረት አለ ብለን ስንነጋገር፣ በመካከላቸው በነበሩ አመለካከቶች ላይ ጥቃቅን ልዩነቶች የነበሩ መሆኑን እውቅና ልትሰጡት ይገባል፡፡ እንደማስበው ዋናው ነገር በመካከላቸው የነበሩት ጥቃቅን የአመለካከት ልዩነቶች መሠረታዊ የሆኑ አስተምህሮዎችን እውነታ ከማረጋገጥ አንጻር ወደመቃረን ያመጣቸው ያልነበረ መሆኑ ነው፡፡ የተለያዩ አመለካከቶች፣ የተለያዩ አትኩሮቶች፣ ስለ እውነታው በተለያየ የንግግር ዘይቤ መናገር እና ስለ እውነታው ልዩ ልዩ ዘርፎች ሊታወጡላቸው የምትችሉበት ሁኔታ ይኖራል፡፡ ግን፣ በእኔ ብይን (ድምዳሜ) ቢያንስ በአዲስ ኪዳን የተለያዩ መጻሕፍት ላይ የከረረ ጠብ ይኖራችኋል ብዬ አላስብም፡፡ [ዶ/ር ዴቪድ ባወር]*

በዚህ የአንድነት ብርሃን መሠረት፣ በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ የተዘረዘሩ የእምነት አንቀጾችን አዲስ ኪዳን ሲያረጋግጣቸው፣ በዓለም አቀፍ ደረጃም ይህንኑ የሚያከናውን መሆኑን መናገር ሚዛናዊነት (አግባብ) ነው፡፡ በፍጹም ባለማወላወል ስለ አብ፣ ስለ ወልድ እና ስለ መንፈስ ቅዱስ መለኮታዊነት የሚሚገት ሲሆን አንድ አምላክ ብቻ መኖሩንም በአጽንዖት ያመለክታል፡፡ ወንጌላቱ ስለ ክርስቶስ አፀናነስ፣ ልደት፣ ሕይወት፣ አገልግሎት፣ ሞት፣ ትንሣኤና ዕርገት የሃይማኖት መግለጫ ጭብጦችን ያቀርባሉ፡፡ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍትም በጠቅላላ የሃይማኖት መግለጫው ስለ ቤተክርስቲያንና ስለ ድነት የሚያቀርበውን አንቀጽ ይደግፉታል፡፡

አዲስ ኪዳንን ከተመለከትን፣ እስኪ እነዚህ የእምነት አቋሞች በቤተክርስቲያን የታሪክ ዘመናት ሁሉ እንዴት የዓለም አቀፋዊው ክርስትና ባሕርያት ሆነው እንደዘለቁ እንመልከት፡፡

## የቤተክርስቲያን ታሪክ

በአዲስ ኪዳን ቀደምት አመታት እንደነበረችው ቤተክርስቲያን ሁሉ፣ በኋለኞቹ ምዕተ ዓመታት የነበረችውም ቤተክርስቲያን በርካታ የነገረ መለኮት ሊቃውንትን አስተናግዳለች፡፡ በበርካቶቹ ጥቃቅን ጉዳዮች ላይ የሚታየው ስምምነት በጣም አናሳ ነው፡፡ ሆኖም ግን በማዕከላውያኑ አስተምህሮዎች፣ እንደ ሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ የእምነት አንቀጾች የመሳሰሉት፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ይሁንታንና ተቀባይነትን አግኝተዋል፡፡ እነዚህ መሠረታዊ የእምነት አቋሞች ቸል

ተብለው በሚገለሉባቸው ጉዳዮች ላይ ቤተክርስቲያንና ታሪክ የተለያዩ አፈንጋጮችን ያስመዘገቡ ሲሆን ጠንካራ መለያየቶችና የስህተት አስተምህሮዎችም ተከስተዋል፡፡

እንደ አንድ ምሳሌ ለመውሰድ ያህል፣ ከክርስቶስ ልደት በኋላ በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተከናወኑትን እንመርምር፡፡ በወቅቱ የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ጥንታዊ ቅጂ በአገልግሎት ላይ ነበር፡፡ በዚህ የታሪክ ዘመን ውስጥ፣ ቤተክርስቲያን በጉባኤዎቿ ምላሽ የሰጠችባቸው ልዩ ልዩ የስህተት አስተምህሮዎች ተነስተው ነበር፡፡ ከነዚህም መካከል አንዳንዶቹ የአጥቢያ ጉባኤዎች ሲሆኑ፣ ሌሎቹ ግን ልዩ ልዩ የሃይማኖት ተቋማትን ያሳተፉ(ecumenical) ነበሩ ምክንያቱም በመላው ዓለም ከሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት የተውጣጡ ጳጳሳት ተሳትፈውባቸው ነበር፡፡ ለአብነትም ያህል፣ የኒቂያው ጉባኤ በ325 ዓ.ም. እና የቁስጥንጥኒያው ጉባኤ በ381 ዓ.ም. የዓለም አቀፍ ሃይማኖቶች ጉባኤዎች (ecumenical) የነበሩ ሲሆን በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ውስጥ ከተካተቱት የእምነት አንቀጾች ጋር ተጓዳኝነት ያላቸውን ጉዳዮች የተመለከቱ ጉባኤዎች ነበሩ፡፡

ዘመናዊው የኒቂያ የሃይማኖት መግለጫ በመጀመሪያ በኒቂያው ጉባኤ በ325 ዓ.ም. ከተነደፈ በኋላ፣ በ381 ዓ.ም. በቁስጥንጥኒያው ጉባኤ ዘመናዊ መልኩን ያዘ፡፡ ይህም የሐዋርያትን የሃይማኖት መግለጫ በሰፊው ያብራራና ሰፋ ባለ መልኩ ያቀረበ ሲሆን፣ ዓላማውም የሃይማኖት መግለጫውን የተሳሳተ ፍቺ ውድቅ ለማድረግ ይቻል ዘንድ የተለያዩ ሃሳቦቹን ማብራራት ነበር፡፡

ለአብነት ያህል፣ ኖስቲሲዝም በመባል የሚታወቀው የስህተት አስተምህሮ መላውን ዓለም የፈጠረው የመጽሐፍ ቅዱሱ እግዚአብሔር ራሱ በሌላ አምላክ (ጣዖት) ተፈጥሯል ብሎ ያስተምራል፡፡ ኖስቲሲዝምን የመሳሰሉ የሃሰት ትምህርቶች በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ተለይተው አልተወገዙም፣ ስለዚህም የኒቂያው የሃይማኖት መግለጫ የሐዋርያትን የሃይማኖት መግለጫ ዓላማ ይበልጥ ግልጥ የሚያደርግ ቋንቋ ተጠቅሟል፡፡

በተለይም፣ የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ "እኔ፣ ሁሉን በሚችል፣ ሰማይንና ምድርን በፈጠረ በእግዚአብሔር አብ አምናለሁ" ብሎ በድፍኑ ያስቀመጠውን፣ የኒቂያው የሃይማኖት መግለጫ ይህንን ሰፋ ያለ መግለጫ ጨምሮበታል፡ እኛ ሁሉን በሚችል በእግዚአብሔር አብ፣ ሰማይንና ምድርን ፣ የሚታዩትንና የማይታዩትን በፈጠረ አንድ አምላክ እናምናለን፡፡ በዚህ ስፍራ የተጠቀሱትን አራት ነገሮች ልብ በሉ፡

በመጀመሪያ፣ የኒቂያው የሃይማኖት መግለጫ በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ የኒቂያው ጉባኤ ተሳታፊዎች ያወጡትን የሃይማኖት መግለጫ በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ላይ በመመሥረት በመላው ዓለም የምትገኘው ቤተክርስቲያን ለሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ይሁንታ የሰጠች መሆኑን በይፋ አሳይተዋል፡፡

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

ሁለተኛ፣ የኒቂያው የሃይማኖት መግለጫ “እኔ” በሚለው ምትክ “እኛ” በማለት ይጀምራል፡፡ የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ እያንዳንዱ ሰው በጥምቀት ወቅት የእምነቱ መግለጫ እንዲያደርገው በሚል ዓላማ ያቀረበው ሲሆን፣ የኒቂያው የሃይማኖት መግለጫ ደግሞ በመላው ዓለም የምትገኘው ቤተክርስቲያን በወል እነዚያኑ አስተምህሮዎች የራሷ እንድታደርጋቸው ዒላማ ተደርጎ የተነደፈ መግለጫ ነው፡፡

ሦስተኛ፣ የኒቂያው የሃይማኖት መግለጫ “አምላክ” ከሚለው ፊት “አንድ” የሚል ማብራሪያ ይሰጣል፡፡ ይህም የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫው ለየት አድርጎ ማመልከት የሚፈልገውን ነገር ማለትም አንድ አምላክ ብቻ እንዳለ ያሳያል፡፡

አራተኛ፣ የኒቂያው የሃይማኖት መግለጫ እግዚአብሔር የማይታዩትን ነገሮች መናፍስትን ጨምሮ ሁሉንም ነገር እንደፈጠረ ማብራሪያ ይሰጣል፡፡ ይህም እግዚአብሔር ፍጡር እንዳልሆነ ያመለክታል፡፡ ይህም ነጥብ እንደገና፣ በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ውስጥ በግልጽ ተቀምጧል፣ ስለዚህም የኒቂያው የሃይማኖት መግለጫ ጉዳዩን ያብራራ ነው ማለት ነው፡፡

በየክፍለ ዘመናቱም ይህንን የመሳሰሉ ማረጋገጫዎችና ማብራሪያዎች በሌሎችም ጉባኤዎችና የነገረ መለኮት ምሁራን መሰጠታቸው ቀጥሏል፡፡ አንዳንድ ጊዜ፣ የጉባኤዎቹ ውሳኔዎች በሁሉም አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ተቀባይነትን አያገኙም፡፡ አንዱ ጉባኤ የአንዳንድ አብያተክርስቲያናትን አመለካከቶች ሲያወግዝ፤ ሌላው ጉባኤ ደግሞ የሌሎቹን አብያተክርስቲያናት አመለካከቶች ያወግዛል፡፡ ሆኖም በአብዛኛዎቹ ጉዳዮች ላይ፣ በነዚህ ሙግቶች ውስጥ ባሉ በሁለቱም ወገኖች የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫው መሠረታዊ መርሆች ይሁንታን ማግኘታቸው ቀጥሏል፡፡

በዚህም ምክንያት፣ የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ እጅግ መሠረታዊ እና ሁሉንም የእምነት ተቋማት የሚያስማማ የክርስትና እምነት አንቀጽ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ በታሪክ ዘመናት መካከል ሁሉንም የእምነት ተቋማት ተቀባይነት ያገኘ እንደሆነ በመገንዘብ የተመለከተው የኒቂያው የሃይማኖት መግለጫ ብቻ ነው፡፡ ሆኖም ግን የኒቂያው የሃይማኖት መግለጫ በራሱ መሠረታዊ አይደለም፡፡ ራሳቸው የነገረ መለኮት ምሁራኑ እንኳን በትክክል የማይገነዘቧቸውን ልዩ ልዩ ነገረ መለኮታዊ መግለጫዎችን አካቷል፡፡ የክርስቲያናዊ እምነት ምሰሶዎችን ከማጥናት አንፃር የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫን የመረጥነው ለዚህ ነው፡፡

ከሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ጋር አዲስ ኪዳን ዓለም አቀፋዊ ስምምነት እንዳለውና በቤተክርስቲያን የታሪክ ዘመናት ሁሉ አስተምህሮዎቹ ተቀባይነትን ማግኘታቸውን ገልጠናል፡፡ አሁን ደግሞ ስለ አሁኑ ዘመን እንነጋገራለን፡፡ ይህም የዘመናችንም ቤተክርስቲያን እነዚሁ የእምነት አቋሞች ብቻ መግለጫዎቿ እንደሆኑ እንመለከታለን፡፡

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

# የአሁን ዘመን

በየትኛውም ዘመን፣ የሃሰት መምህራን ቤተክርስቲያን ለበርካታ ምዕተ ዓመታት የያዘቻቸውን መሠረታዊ የእምነት አቋሞች ይክዳሉ፡፡ በዘመናዊውም ዓለም፣ እንደ የይሖዋ ምስክሮችና ሞርሞኖችን የመሳሰሉ የሃሰት እምነቶች መጽሐፍ ቅዱስን ስለሚቀበሉና ክርስቶስን በውስን መንገድ እንከተላለን ብለው ስለሚያስቡ ራሳቸውን እንደ ክርስቲያን ይቆጥራሉ፡፡ ሆኖም ግን እውነተኛ ክርስቲያኖች አይደሉም ምክንያቱም ለሁለት ሺህ ዓመታት የክርስትናን ድንበር የሚያመለክቱትንና በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ውስጥ የተቀመጡትን መሠረታዊ የእምነት አቋሞች ይክዳሉና፡፡ እንዲያውም ከሃሰተኞቹ ጎራ ያልተመደቡ አንዳንድ ቤተክርስቲያናት እና በክርስቲያን ቤተክርስቲያን ውስጥ የሚገኙ ግለሰብ አስተማሪዎችም ጭምር በተመሳሳይ መንገድ እነዚህን መሠረታዊ የእምነት አቋሞች ይክዳሉ፡፡

በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ውስጥ የተዘረዘሩትን አስተምህሮዎች በርካታ ሰዎች ውድቅ ካደረጉዋቸው፣ የሃይማኖት መግለጫው በአሁን ዘመን የምትገኘው ቤተክርስቲያን ዓለም አቀፋዊ መገለጫ ነው ማለት እንዴት እንችላለን? መልሱ መንታ ነው፡፡ በአንድ በኩል፣ ክርስትናቸውን ያረጋገጡ አብዛኞቹ አብተክርስቲያናት እነዚህን አስተምህሮዎች ይሁንታ ሰጥተዋቸዋል፡፡ ሁሉም ዓይነት ወግ አጥባቂ ፕሮቴስታንቶች ማለትም ባፕቲስቶች፣ ሜቶዲስቶች፣ ሉትራኖች፣ አንግሊካኖች፣ ፕሬስቢቴሪያኖች፣ ወ.ዘ.ተ. ያምኑባቸዋል ትምህርትም ይሰጥባቸዋል፡፡ በተጨማሪም ፕሮቴስታንት ባልሆኑ በታላላቅ አብያተክርስቲያናት ማለትም የሮማ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያንና የምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተክርስቲያናትም ዘንድ ይሁንታን አግኝተዋል፡፡

ከዚህ ውጪ፣ እነዚህን አስተምህሮዎች የሚክዱ አብያተክርስቲያናት “ክርስቲያን” ተብለው ሊጠሩ አይገባም፡፡ ምንም እንኳን መጽሐፍ ቅዱስን እንደሚቀበሉና ክርስቶስን እንደሚከተሉ ቢናገሩም፣ በእውነት ግን የቅዱሳት መጻሕፍትን ወይንም የታሪካዊቷን ቤተክርስቲያን ትምህርቶች የራሳቸው አድርገው አይይዙም፡፡ በዚህም ምክንያት፣ በእውነት ክርስቲያኖች አይደሉም፡፡

> *በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ውስጥ ስለ ተጠቀሱት አስተምህሮዎች አስፈላጊነት በምናስብበት ወቅት፣ እነዚህ ነገሮች ለቤተክርስቲያን ሕይወት፣ የወንጌልን ተፈጥሮ ለመገንዘብና በክርስቶስ ያገኘነውን መዳን ለመረዳት እጅግ ወሳኝ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ያህል፣ የሃይማኖት መግለጫው የእግዚአብሔርን የስላሴ ባሕርይ ያውጅልናል፡ እግዚአብሔር አብ ነው፣ እግዚአብሔር ወልድ ነው፣ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ እንግዲያው፣ ክርስቲያን ነን ካልን፣ ስላሴ አንድ የሆነ ግሩም ጣዕመ ዜማ የምናሰማበት በእምነታችን ላይ የምንቀባው ማድመቂያ እንደሆነ ልናስመስል አይገባንም፡፡ ይልቁኑ የስላሴ አስተምህሮ የእኛ*

*አምላክ በእውነት ማን እንደሆነ፣ ማንነቱን የምንረዳበት መግለጫ ነው፡፡ [ዶ/ር ስቲቭ ብላክሞር]*

*በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ውስጥ የሚገኙት አስተምህሮዎች ለክርስትና መሠረታዊና እጅግ ወሳኝ ናቸው ማለት እወዳለሁ፡፡ ከእነርሱ ዘወር ካላችሁ፣ ከታሪካዊው የክርስትና እምነት የተለያችሁ መሆኑ እርግጥ ነው፡፡ ይህ ነገር የቀድሞዋ ቤተክርስቲያን ልምድ ነበር፣ መጽሐፍ ቅዱስ ይተረጎምባቸው የነበሩ እጅግ የተለያዩ መንገዶች እንደነበሩ ደረሱበት ስለዚህም "ትክክለኛው መንገድ ይህ ነው" አሉ፡፡ ጉዳዩ ልክ እንደ ባቡር ሃዲድ ነው፡ "መጽሐፍ ቅዱስ ሊፈታበት የሚገባ ትክክለኛ መስመር ይህ ነው" እንደ ማለት ነው፡፡ ከዚያ በተቃራኒ መንገድ ከሄዳችሁ ከወሳኙ የክርስትና እምነት መገንጠላችሁ ነው፡፡ እናም እስከዚህ ዘመን ድረስ የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ፣ የእውነተኛውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት ተፈጥሮ የሚያብራራ ነው ብዬ አስባለሁ፡፡ [ዶ/ር ፒተር ዎከር]*

በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ውስጥ ተጠቃለው የቀረቡት የእምነት አቋሞች መሠረታዊና ዓለም አቀፋዊ በመሆናቸው ምክንያት፣ በአማኞች መካከል የአንድነት ተፅዕኖ ፈጣሪ ሆነዋል፡፡ በተለይም በዚህ ዘመን ይህ ጉዳይ እጅግ ዋጋ የሚሰጠው ነገር ነው ምክንያቱም በዘመናችን ቤተክርስቲያን ውስጥ ብዙ መከፋፈል አለ፡፡

## አሃዳዊ / አንድነት

ምናልባት ነገረ መለኮት መማርን የሚቃወሙ እውነተኛ ክርስቲያኖች ገጥመዋችሁ ይሆናል ምክንያቱም አስተምህሮዎች ክርስቲያኖችን እርስ በርስ መከፋፈል ብቻ እንጂ ሌላ ፋይዳ የላቸውም ብለው ስለደመደሙ ነው፡፡ መደበኛውን የነገረ መለኮት ትምህርት [ኢየሱስ አንድ ያደርገናል፣ አስተምህሮዎች ግን ይለያዩናል] በሚል መፈክር ተቃውሟቸውን ያስፋፉሉ፡፡ በዚህ አቋም ላይ ቀላል ነው የማይባል እውነት አለ፡፡ በየዘመናቱ ክርስቲያኖች እርስ በርሳቸው ተለያይተዋል፣ እርስ በርስ ተወነጃጅለዋል፣ አንዱ ሌላውን አሳዷል እንዲያውም በተለያዩ አስተምህሮቶች ምክንያት ጦር ተማዝዘዋል፡፡ ይህም ሆኖ ግን፣ አዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን አሁንም ቢሆን ለአስተምሮታዊ አንድነት እንድትተጋ ያበረታታል፡፡ ለአብነት ያህል ኤፌሶን 4፥11-13 እነዚህን ቃላት እናነብባለን፡

> እርሱም አንዳንዶቹ ሐዋርያት፥ ሌሎቹም ነቢያት፥ ሌሎቹም ወንጌልን ሰባኪዎች፥ ሌሎቹም እረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ፤ ሁላችን የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኝ አንድነት፥ ሙሉ ሰውም ወደ መሆን፥ የክርስቶስም ሙላቱ ወደሚሆን ወደ ሙላቱ ልክ እስክንደርስ ድረስ፥ ቅዱሳን አገልግሎትን ለመሥራትና ለክርስቶስ አካል ሕንጻ ፍጹማን ይሆኑ ዘንድ።

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

በዚህ ምንባብ፣ ጳውሎስ ቤተክርስቲያንን በአካል ይመስላታል፡፡ እኛ በእምነት እና በእውቀት አንድ እስካልሆንን ድረስ ቤተክርስቲያን ወደ ብስለት እንደማትደርስ አመልክቷል፡፡ በዚህ ምክንያት አስተምህሮታዊ አንድነት የሁሉም ክርስቲያን ግብ ሊሆን ይገባዋል፡፡

በእርግጥ፣ የአስተምህሮት ጥናታችንን ሌሎቹ በርካታ የክርስትና ሕይወት ዘርፎች ሊቀርጹት ይገባል፡፡ እግዚአብሔርንና ባልንጀራን መውደድ፣ ቅድስናን መከታተል፣ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል መደገፍ፣ እግዚአብሔርን ማሰብና ቃሉን ማሰላሰልን የመሳሰሉ ተግባራትን ማከናወን ያስፈልገናል፡፡ በአስተምህሮት ላይ ብቻ አትኩረን ሌሎቹን ጉዳዮች ቸል ብንል፣ ደግመን ደጋግመን አሳዛኝ በሆነ መንገድ ከመንገዱ የምንወጣ እንሆናለን፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ቆሮ 13፥2 እንዳስጠነቀቀው፡

> ትንቢትም ቢኖረኝ ምሥጢርንም ሁሉና እውቀትን ሁሉ ባውቅ፥ ተራሮችንም እስካፈልስ ድረስ እምነት ሁሉ ቢኖረኝ ፍቅር ግን ከሌለኝ ከንቱ ነኝ።

ይህ ጥቅስና ሌሎችም በርካቶች እንደሚያመለክቱት፣ ነገረ መለኮታዊ እውቀት ማግኘት አስፈላጊ ነው፣ ነገር ግን የክርስትና እምነት የመጨረሻው መልካም ነገር አይደለም፡፡

የነገረ መለኮታዊ እሰጥ አገባን አፍራሽ መዘዞች ለማስወገድ ፍቱን የሆነው መንገድ በመላው ዓለም የሚገኙ የክርስቶስን ተከታዮች ሁሉ በአስተምህሮታዊ አንድነት ደስ ሊያሰኝ በሚችል አካሄድ ማከናወን ነው፡፡ ለነገረ መለኮት ጥልቅ ጉዳዮች የምንሰጠውን ትኩረት ከትክክለኛው የአንድነት መሻት ጋር ሚዛናዊ ካደረግነው፣ በአስተምህሮ ከመከፋፈል ይልቅ አንድ ያደርገናል፡፡

> *የዛሬዋ የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ለአንድነት ግድ የሚላት ነች፡፡ በርካታ ቤተ እምነቶች አሉን በመንፈስ ቅዱስ፣ በሴቶች፣ በጥምቀት የተለያዩ አመለካከቶች አሉን፡፡ ሆኖም ዛሬ በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን በጣም የምናተኩረው እውነትን መሠረት ካደረገ ነገር ይልቅ ዓለምን በመድረሱ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ላይ ነው፡፡ ጌታችን ኢየሱስ እና ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ እኛ አንድነት ሲያስቡ (እያሰብኩ ያለሁት የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 17 እና ኤፌሶን ምዕራፍ 4 ነው) የሚያስቡት አንድ አምላክ፣ አንድ ጌታ፣ አንድ መንፈስ፣ አንድ እምነት፣ አንድ ጥምቀት ያለን ስለ መሆኑ ነው፡፡ በክርስቶስ ላገኘነው አንድነት መሠረቱ ሊሆን የሚገባው እውነቶቹ ወይንም የምናምንበት እውነት አካል ብቻ ነው፡፡ [ዶ/ር ሳሙኤል ሊንግ]*

በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ውስጥ ለተገለጡት ማዕከላዊ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርቶች ራሳቸውን በፅኑ የሰጡ በመቶ ሚሊዮኖች የሚቆጠሩ እውነተኛ የክርስቶስ ተከታዮች በመላው ዓለም ይገኛሉ፡፡ እርግጥ ነው፣ በዚህ አሁን ባለንበት ወቅት እንኳን አያሌ ክርስቲያኖች ስለዚህ

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

መሰጠታቸው በስደት ይሰቃያሉ እንዲያውም መስዋዕትም ይሆናሉ፡፡ በሌሎች በበርካታ ነገረ መለኮታዊ ጉዳዮች ከእኛ ጋር አይስማሙም፡፡ እንዲያውም፣ እኛ በጣም አክብረን የያዝናቸውን አመለካከቶች በብርቱ ሊቃወሟቸው ይችላሉ፡፡ ሆኖም እነዚህ ሁሉ ልዩነቶቻችን ሳይገድቡን የሃይማኖት መግለጫው ስለ እግዚአብሔር፣ ስለ ቤተክርስቲያንና ስለ ድነት በሚናገረው በአንድነት ልንቆም ይገባል፡፡ ኢየሱስ በዮሐንስ 17፥23 ለቤተክርስቲያን የጸለየውን አስታውሱ፡

> እኛም አንድ እንደ ሆንን አንድ ይሆኑ ዘንድ፤ እኔም በእነርሱ አንተም በእኔ ስትሆን፥ በአንድ ፍጹማን እንዲሆኑ፥ የሰጠኸኝን ክብር እኔ ሰጥቻቸዋለሁ፤ እንዲሁም ዓለም አንተ እንደ ላክኸኝ በወደድኸኝም መጠን እነርሱን እንደ ወደድሃቸው ያውቃል።

በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚገለጥ አንድነት ኢየሱስ በአብ የተላከ መሆኑን እንደሚያረጋግጥ ኢየሱስ መናገሩን ልብ በሉ፡፡ ከሌሎቹ የክርስቶስ ተከታዮች ጋር የጋራችን በሆኑ ነገረ መለኮታዊ መረዳቶች ላይ ትከሻ ለትከሻ ተያይዘን ስንቆም፣ ወንጌል እውነት መሆኑን ለዓለም የምንመሰክር ሲሆን፣ ይህም የወንጌል ተልዕኳችንን ጉልበታም ያደርገዋል፡፡

> *ወንጌልን በማብራራትና የጋራችን በሆኑት የወንጌል እውነቶች ላይ በመስማማት፣ እውነትንና አንድነትን የምንከታተልበት አንዱ መንገድ በወንጌል ውስጥ ለሚገኘው አንድነት ራሳችንን መስጠታችንን ማወጅ ማለት እንደሆነ አስባለሁ፡፡ በዚህ መንገድ አርስ በርስ የሚኖረንን አንድነት በሕይወትና በአገልግሎት በመከታተል ለእምነታችን ያለንን ቁርጠኝነት ከድርድር ውስጥ አናስገባም ወይንም ተወት አናደርገውም ማለት ነው፡፡ ይህንን አንድነት ደስ የምንሰኝበት አንዳችን ከሌላችን በምንለያይባቸው ነገሮችም እንኳን ሳይቀር ነው፡፡ በመከባበር በጥቃቅን ጉዳዮች ልንለያይ እንችላለን፡፡ በፍጹም እውቀት ልንለያይ እንችላለን፡፡ በፍቅር አንዳችን ከሌላችን ልዩነት ሊኖረን ይችላል፡፡ ይህም ሆኖ ግን በእውነትና በአሳማኝ ደረጃ ለሁላችን የጋራ ደስታ የሚያስገኙልንን ነገሮች መመልከት ይኖርብናል፡፡ እነዚህንም ነገሮች በተወሰነ ደረጃ ደስ እንሰኝባቸዋለን፣ ስለዚህም አንድነት ደስ የምንሰኝበት ይሆናል እናም በሌሎቹ ነገረ መለኮታዊ ጉዳዮቻችን ላይ ሕጋዊ እና በእውነተኛ ሕሊና የሚመራ ልዩነት ሊኖረን ይችላል፡፡ [ዶ/ር ጄ. ሊጎን ዱካን ሳልሳዊ]*

የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ በየትኛውም ስፍራ የሚገኙ ክርስቲያኖች ወሳኝ በሆኑት የእምነት አቋሞችና መለስተኛ ጠቀሜታ ባላቸው የእምነት አቋሞች መካከል እንዲለዩ ይረዳቸዋል፡፡ ይህንን የሃይማኖት መግለጫ በግል ሕይወታችንና በቤተክርስቲያን የጋራ ሕይወታችን ጠበቅ አድርገን ከያዝን፣ ነገረ መለኮት አንዳችንን ከሌላችን አይለያየንም፡፡ በምትኩ እንዲያውም፣ ከሌሎቹ ታማኝ የክርስቶስ አገልጋዮች ጋር እንተባበራለን፣ በዚህም ኢየሱስ ለራሱ ቤተክርስቲያን ያለውን ራእይ እናሳካለን፡፡

# ማጠቃለያ

የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫን የእምነት አንቀጾች መግቢያ በሰጠንበት በዚህ ትምህርት ውስጥ፣ የሃይማኖት መግለጫውን ታሪክ ከግንባታና ከዓላማ አንፃር ተነጋግረንበታል፡፡ ከእግዚአብሔር፣ ከቤተክርስቲያንና ከድነትም አንፃር የአስተምህሮውን ወፍ በረር ዳሰሳ አድርገናል፡፡ የእምነት አንቀፆቹንም ጠቀሜታ ከመሠረታዊነታቸው፣ ከዓለምአቀፋዊነታቸውና ከአሃዳዊ ተፈጥሮአቸው አንፃር ቃኝተናል፡፡

የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ በመቶዎችን በሺዎች ለሚቆጠሩ ዓመታት የክርስትናን ማዕከላዊ ክርስቲያናዊ የእምነት አቋሞችን አጠቃሎ የያዘ ጠቃሚ ታሪካዊ ሰነድ ነው፡፡ በዛሬውም ዘመን እንኳን፣ በሁሉም ቤተ እምነቶች ለሚገኙ ክርስቲያን የነገረ መለኮት ምሁራን አንድ የሆነ የመነሻ ነጥብ መስጠቱን እንደቀጠለ ነው፡፡ በዚህ ተከታታይ ትምህርት ቀጥለው በሚመጡት ትምህርቶች የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫውን የእምነት አንቀፆች በበለጠ ጥልቀት፣ በመላው ዓለም የሚገኙ ክርስቲያኖችን አንድ በሚያደርግ መንገድ የቅዱሳት መጻሕፍትን እውነቶች እንዴት እንደሚወክሉ እንዳስሳቸዋለን፡፡

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org